
የሽግግር ፍትህ
TRANSITIONAL JUSTICE




# የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ

# ETHIOPIA
# TRANSITIONAL JUSTICE IMPLEMENTATION ROADMAP (FINAL)

የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር

ነሐሴ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

**ማውጫ**


1. መግቢያ 2
2. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ጠቀሜታ እና አላማ 3
3. የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ 4
4. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች (ወሰን) 4
5. በፍኖተ-ካርታው ላይ የተመላከቱ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎች የሚመሩባቸው መርሆች 4
6. የሽግግር ፍትህ ትግበራ የተቀናጀ ተቋማዊ አመራር 4
   - 6.1. የተቋማዊ አደረጃጀት አላማ እና አስፈላጊነት 4
   - 6.2. የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ አባላት እና ዝርዝር ሀላፊነቶች 5
   - 6.3. የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጀት 6
7. በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች ተመጋጋቢነት እና ቅደም-ተከተልን የሚመለከቱ ጉዳዮች 7
   - 7.1. በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል ውድድር ለማስቀረት/ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት 7
   - 7.2. የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል እቅድ 7
8. ህዝባዊ ገፅታ የማላበስ/የማንቃት እና መደበኛ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች የሚከናወኑበት አግባብ 8
9. ሕጎች የማውጣት ስራ 12
   - 9.1. አዲስ የሕግ ማዕቀፍ የሚወጣለት ጉዳይ እና የረቂቅ ዝግጅት 12
   - 9.2. የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ዝግጅት 13
10. የሽግግር ፍትህ ተቋማት አቅም ግንባታ ስራ 17
11. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ለመለየት/ለማሳለጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች 20
    - 11.1. መግቢያ 20
    - 11.2. ክልሎች በሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ የሚኖራቸው ሀላፊነት 20
12. የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች ሚና 21
13. ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለመለየት/ለማስፈፀም የሚከናወኑ ተግባራት 22
    - 13.1. አጠቃላይ ስራዎች 22
    - 13.2. ለፆታ ጥቃት ሰለባዎች ልዩ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ተጨማሪ እርምጃዎች 23
14. የሽግግር ፍትህ ትግበራ መረጃዎች የሚያዙበት፣ የሚደራጁበትና ተደራሽ የሚሆኑበት የመረጃ ቋት ስርዓት 23

**አባሪ** 1: የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ (Sequenced Implementation – Master-Deck) 25

## 1. መግቢያ

በኢትዮጵያ የሚካሄደው ሁሉ-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ሥርዐት ግንባታ ስራ ወደ አዲስ ምዕራፍ የሚሸጋገርበት ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ህዳር 2015 ዓ.ም የኢትዮጵያ መንግስት በወንጀል ተጠያቂነት፡ በእውነት ማውጣት፡ በምህረት፡ በእርቅ፡ በማካካሻ እና ተቋማዊ ማሻሻያ መርሆች ላይ የተዋቀረ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ለመተግበር ይፋዊ እንቅስቃሴ መጀመሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ውሳኔ ማዕቀፍ የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን እንዲቋቋም የተደረገ ሲሆን - ቡድኑ ሰፊ የህዝብ ግብዐት ማሰባሰቢያ መድረኮችን በማዘጋጀትና ምክክሮችን በማካሄድ ታህሳስ 19 2016 ዓ.ም **'የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ የፖሊሲ አቅጣጫ አማራጮች - የህዝብ ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት'** ይፋ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም **'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ'** ረቂቅ ሰነድ በማዘጋጀት ጥር 2016 ዓ.ም ለመንግስት አስረክቧል፡፡

በቀጣይም የኢፌዲሪ ፍትህ ሚኒስቴር ከየካቲት 13-17 2016 ዓ.ም ባለው ጊዜ በረቂቅ ብሄራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር አራት የማጠናቀቂያ ምክክር መርሀ-ግብሮችን አካሂዷል፡፡ በዚህ ረጅም፡ አሳታፊ እና አካታች የዝግጅት ሂደት ባለፈ ሰነድ ላይ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በ30ኛ መደበኛ ስብሰባው ዝርዝር ውይይት ካካሄደ በኋላ ሚያዝያ 9 2016 ዓ.ም **'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን'** አፅድቋል፡፡

ይህን ተከትሎም ፖሊሲው ወደ ትግበራ ምዕራፍ የሚሸጋገርበት የዝግጅት ስራ ተጀምሯል፡፡

ይህ ፍኖተ-ካርታ የተዘጋጀው 'የፖሊሲውን አፈፃፀም፡ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓትን' በተመለከተ ሁሉም የስራ ሂደቶች በሚፈለገው አግባብ እንዲተገበሩ - ዝርዝር አካሄዶችን የሚመራ 'የፖሊሲ አፈፃፀም ፍኖተ ካርታ' የሚዘጋጅ ስለመሆኑ ፖሊሲው ያስቀመጠውን የአፈፃፀም አቅጣጫ መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## 2. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ጠቀሜታ እና ዓላማ

በኢትዮጵያ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ሰነድ መፅደቁ ታላቅ አገራዊ ክንዋኔ ቢሆንም - ይህ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ አገራዊ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ግንባታን ለማረጋገጥ በቀጣይ ምዕራፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች ወሳኝ ናቸው፡፡

የሽግግር ፍትህ ትግበራ በባህሪው ከፍተኛ የተቋማት ትብብር፡ ቅንጅትና የክትትል እና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በፀደቀው የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም፡ የተሟላ ፍትህ፡ እርቅና የሕግ የበላይነት የማስፈን ግብ የበርካታ ባለድርሻ አካላትን ሚና እና ሀላፊነት መዘርዘር፡ የስራ ሂደቶቻቸውን እና የጊዜ ማዕቀፎችን በግልፅ ማመላከት፡ እና የሀብት አሰባሰብ እና አጠቃቀም ስራ የሚቀናጅበትን አግባብ ማሳየት የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው፡፡

በመሆኑም በፖሊሲው ላይ የተመላከቱ ተቋማት ተደራጅተው ስራቸውን እስኪጀምሩ ድረስ፡ እንዲሁም ስራ ከጀመሩ በኋላም ቢሆን ተቀናጅተውና ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ለማድረግ የሽግግር ፍትህ ትግበራን የሚመራ ሁሉን-አቀፍ ፍኖተ-ካርታ አስቀድሞ ማዘጋጀት ተገቢ ነው፡፡ የፍኖተ-ካርታ መኖር ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባራት በትብብርና በተናበበ መንገድ መምራት የሚችሉበትን እድል ይፈጥራል፡፡ እንደአገር ውሳኔ ያረፈባቸው የሽግግር ፍትህ አምዶችን በተሻለ ግልፅነት፡ ተገማችነት፡ ወቅታዊነትና ውጤታማነት መሬት ላይ ለማውረድ እና ለመተግበር ፍኖተ-ካርታ ቁልፍ መሳሪያ ነው፡፡

ከስነ-ዘዴ አንፃር የዚህ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ስራ - የአፍሪካ ህብረት ግንቦት 2020 (እ.ኤ.አ) ባወጣው የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ ላይ የተንፀባረቁ ውስን ሀሳቦችን፣[1] እንዲሁም በዚህ ረገድ ጥቂት አገራት የተገበሩትን አሰራር ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ሙከራ አድርጓል።

በሚቀጥሉት ወራትና አመታት በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረገውን የሽግግር ፍትህ ሥርዓት አፈፃፀም የሚመራው ይህ 'የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ' የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎች ይኖሩታል።

- በፖሊሲው ላይ በመመርኮዝ በቀጣይ ተግባራዊ የሚደረጉ ዋና ዋና ስራዎች (activities)፣ ስራዎቹ የሚከናወኑበት የጊዜ ሰሌዳ፣ እና የሚጠበቁ ዋና ዋና ውጤቶች (outcomes) በዝርዝር ማመላከት፣
- ፖሊሲውን በተገቢ ደረጃ፣ መጠንና ጥራት ለማስፈፀም የሚያግዙ ሰነዶችና ዋና ዋና ስራዎች ዝግጅት የሚሳለጥበትን ሂደት/አሰራር (processes/procedures) በዝርዝር ማስቀመጥ፣
- በፖሊሲው የተለያዩ ክፍሎች ትግበራ ሂደት ባለድርሻ ተቋማት የሚኖራቸውን ሚና ወይም ሀላፊነት በግልፅ ማሳየት፣
- በተለያዩ ባለድርሻ አካላት እና የጊዜ ማእቀፎች የሚከናወኑ ቀጣይ ስራዎች በተቀናጀ፣ በተመጋገበ እና ባልተፋለሰ መንገድ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ተግባራዊ የሚደረጉበትን አሰራር መመስረት፣
- ፖሊሲውን ለመተግበር የሚወሰዱ እርምጃዎች አጠቃላይ አፈፃፀም የሚመራበት፣ የሂደቶች አንኳር ፍፃሚዎች በምክክር የሚገመገሙበት እና ምልከታዎች የሚጋሩበት ቋሚ ተቋማዊ አሰራር ማመላከት፣
- እንዲሁም ለፖሊሲው ትግበራ የሚያስፈልግ ሀብት ምንጭ፣ የሀብት ዝርዝር እና የመንግስትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ሀላፊነትን ማመላከት ናቸው።

## 3. የትግበራ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ

ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲው መሰረት የሆነው አገር-አቀፍ የህዝብ ምክክርና ግብዓት ማሰባሰብ ስራ - የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባዎችን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን ጨምሮ - ከፍተኛ የህዝብ እና ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ያረጋገጠ ሂደት ነበር። የፖሊሲው ረቂቅ የመጨረሻ ቅርፁን የያዘው በተመሳሳይ የህዝብ እይታና አስተያየት ሂደት አልፎ ነው።

የዚህ አይነቱ አሰራር መሰረታዊ መልእክት የትኛውንም የሽግግር ፍትህ ክፍል የሚመለከት የስራ ሂደት የሁሉም ባለድርሻ አካላት ሙሉ እና ትርጉም ያለው ተሳትፎ እና የህዝብን ወሳኝነት በሚያረጋግጥ አግባብ ሊከናወን ይገባል የሚል ነው። የሽግግር ፍትህን የሚመለከቱ ስራዎችን - ከመሰረታዊ የመሳተፍ ሰብአዊ መብት መርህ ጋር በተጣጣመ አግባብ በዚህ መንገድ ማሳለጥ - በፖሊሲው እና ፖሊሲውን ተከትሎ በሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች አንፃር የህዝቡን ሙሉ እምነት ለመግዛት፣ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎችን ጨምሮ ለሰፊው ማህበረሰብ ድምፅና የፍትህ እና የሰላም ተስፋ እውቅና ለመስጠት፣ የሂደቱን አጠቃላይ ቅቡልነት ለማስፋትና ዘለቄታዊ ውጤታማነቱን ለማረጋገጥ አይነተኛ ሚና ይኖረዋል።

በመሆኑም በዚህ ፍኖተ-ካርታ ዝግጅት ሂደት ተመሳሳይ የአካታችነትና አሳታፊነት መርሆች ተግባራዊ ተደርገዋል። የመንግስት፣ የህዝብና የመብት ጥሰት ሰለባዎች እይታ እና ድምፅ በተሻለ መንገድ እንዲወከል ከማድረግ አንፃር የፍኖተ-ካርታው ዝግጅት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት በተውጣጣ ቡድን እንዲከናወን ተደርጓል። በስራው የቀድሞ

[1] African Union. Roadmap for the Implementation of the African Union Transitional Justice Policy. May 2020. Addis Ababa. Ethiopia.

የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎች ቡድን አራት አባላትን ጨምሮ፡ ከኢፌዴሪ ፍትህ ሚኒስቴር (2)፡ ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን (1) እና ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች (2) የተውጣጡ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል።

በረቂቅ ፍኖተ-ካርታው ላይ ሁለት አገር-አቀፍ የውይይትና የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች በአዲስ አበባ ከተማ ተዘጋጅተዋል። የመጀመሪያው መድረክ ሰኔ 26 2016 ዓ.ም ከመንግስት ተቋማት አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር የተካሄደ ሲሆን፡ ሁለተኛው ሰኔ 27 2016 ዓ.ም ከዓለም-ዐቀፍ ተቋማት እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተከናውኗል። ውስን ተቋማትም በረቂቁ ላይ ያላቸውን ምልከታ በፅሁፍ አጋርተዋል። በመድረኮቹ እና የፅሁፍ ሰነዶቹ ላይ የተንፀባረቁ ሀሳቦች እንደአግባብነቱ በዚህ ፍኖተ-ካርታ የመጨረሻ ይዘት ላይ እንዲካተቱ ተደርጓል።

## 4. የሽግግር ፍትህ ትግበራ ፍኖተ-ካርታ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች (ወሰን)

ይህ ፍኖተ-ካርታ 'የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲን' ለማስፈፀም በየትኛውም መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ባልሆነ አካል በሚወሰዱ አሁናዊ ወይም ቀጣይ የሕግ፡ የተቋም ወይም የአሰራር ሥርዓት ወይም ተግባራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ፍኖተ-ካርታው በብሄራዊ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ማዕቀፍ - ክልሎች በአገር-አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ ስራዎችን አስመልክቶ በተሰጧቸው እገዛ የመስጠት፡ የትብብር እና የቅንጅት ግዴታዎች ላይ ሙሉ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው አጠቃላይ እሳቤዎችና መርሆዎች ላይ በመመስረት ስራዎችን የመምራት ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ - ክልሎች በአገራዊ የሽግግር ፍትሕ የስራ ሂደት የማይሸፈኑ ጉዳዮችን፡ ጥሰቶችን እና ግጭቶችን በተመለከተ በባለቤትነት በሚያከናውኗቸው ውስን የእውነት ማፈላለግ/ይፋ ማውጣት፡ የዕርቅ እና የማካካሻ ስርዓት ስራዎች ላይ የራሳቸውን ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት ይችላሉ።

## 5. በፍኖተ-ካርታው ላይ የተመላከቱ የሽግግር ፍትህ ትግበራ ስራዎች የሚመሩባቸው መርሆች

በፍኖተ-ካርታው ላይ በመመስረት የሚከናወን ማናቸውም የፖሊሲ ትግበራ ሂደት አግባብነት ባላቸው ዓለም-አቀፍና አህጉር-አቀፍ ሰነዶች እና በብሔራዊ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በተቀመጡ መርሆዎች እና እሴቶች የሚመራ ይሆናል። በመሆኑም በቀጣይ ክፍሎች የተቀመጡ የትግበራ ስራዎች አቀራረፅ እና አፈፃፀም፥

- የተሳታፊዎች እና ተጎጂዎችን ደህንነት በሚጠብቅ፡
- ከዳግም ጥቃት የመጠበቅ መብትን በሚያረጋግጥ፡
- ሁሉንም የማህበረሰብ ክፍሎች እና ቁልፍ ባለድርሻ አካላትን በሚያካትት እና በሚያሳትፍ፡
- ተጠያቂነት እና ሁሉን-አቀፍ ፍትህን በሚያሰፍን፡
- ለስርአተ-ጾታ ምልከታ ልዩ ቦታ በሚሰጥ፡
- የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ በሚያስገባ፡
- የተለያዩ የሽግግር ፍትህ አላባዎችን በተቀናጀ፡ በተናበበ እና ቅደም-ተከተልን በጠበቀ አግባብ በሚመራ፡
- ለህዝብ ባለቤትነት እና ለአገር ውሳኔ ሰጪነት ልዩ ትኩረት በሚሰጥ፡
- እንዲሁም አገራዊ እና አካባቢያዊ ሁነቶችን ግምት ውስጥ በሚያስገባ አግባብ የሚከናወን ይሆናል።

## 6. የሽግግር ፍትህ ትግበራ የተቀናጀ ተቋማዊ አመራር

### 6.1. የተቋማዊ አደረጃጀት ዓላማ እና አስፈላጊነት

በተለያዩ የጊዜ ማዕቀፎች የሚከናወን አገራዊ የሽግግር ፍትህ ስራ የብዙ ተቋማትን ትብብርና ቅንጅት የሚጠይቅ ውስብስብ ሂደት ነው። የሰመረ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ግንኙነትና አሰራር ሲታሰብ ለዚህ አላማ አንድ ወጥ የቅንጅት አመራር መመስረትና የሚኖረውን ተግባርና ሀላፊነት መዘርዘር ተገቢ ይሆናል።

በመሆኑም፥

- በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ የተመላከቱ ተቋማት በህግ እስኪቋቋሙና ኃላፊነቶቻቸውን ሙሉ ለሙሉ እስኪረከቡ ድረስ ባለው የጊዜ ማዕቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎችን የሚከታተል እና የሚያስተባብር፣
- እንዲሁም በፖሊሲው ላይ የተመላከቱ አዳዲስ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት ከተቋቋሙ በኋላ አጠቃላይ የትግበራ ሂደቱን አፈፃፀም በዘላቂነት የሚያቀናጅ፣ የሚያስተባብርና የሚከታተል፣ ሂደቱን እየገመገመ የጋራ እይታ የሚያስቀምጥ፣

'የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' (Transitional Justice - Institutional Coordination Mechanism) ይቋቋማል።

## 6.2. የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ አባላት እና ዝርዝር ሀላፊነቶች

'የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ' በየተቋማቱ ከፍተኛ አመራሮች የሚወከሉ 13 አባላት ይኖሩታል።

አደረጃጀቱ ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (2)፣ ከፍትህ ሚኒስቴር፣ ከፌዴራል ፍርድ ቤት፣ ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከገንዘብ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ ወደፊት ከሚደራጁ ሶስት ተቋማት (3)፣ እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እና አካዳሚያ (2)[2] የሚወከሉ አባላትን የሚያካትት ይሆናል።

- አደረጃጀቱ ከአባላቱ መካከል የሚሰየሙ ሰብሳቢ እና ፀሀፊ ይኖሩታል።
- በሂደት በሌላ አማራጭ እስከሚተካ ድረስ በፍትሕ ሚኒስቴር የሚገኘው የሰብአዊ መብቶች ክትትል ዳይሬክቶሬት የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት በመሆን ያገለግላል።
- የዚህ አደረጃጀት የቆይታ ጊዜ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ስራ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል።
- የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በየሶስት ወሩ ይገናኛል።

**የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ የሚከተሉት ዝርዝር ሀላፊነቶች ይኖሩታል።**

- አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት የማቋቋሚያ ሕጎች ረቂቅና የአሰራር ሥርአት ሰነዶች (ደንቦች፣ መመሪያዎች ወዘተ) በባለሙያዎች ተዘጋጅተው ሲቀርቡ ይገመግማል፣ ምክረ-ሀሳብ ያቀርባል፣
- አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትሕ ተቋማት በፍኖተ-ካርታው ላይ በተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ መቋቋማቸውን እና መደራጀታቸውን ይከታተላል፣
- ለሽግግር ፍትሕ ትግበራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ መነሻ ጥናቶች ሲቀርቡ ይገመግማል፣ ሀሳብ ይሰጣል፣
- በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚከናወኑ የህዝብ ግንዛቤ ፈጠራ ሥራዎችን ይደግፋል፣

[2] ከሲቪል ማህበረሰብ (አካዳሚያ እና የፖሊሲ ምርምር ተቋማትን ጨምሮ) የሚወከሉ 2 አባላት - የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን እና የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሚያስተባብሩት አገር አቀፍ መድረክ የሚመረጡ ይሆናል።

- ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት ኃላፊዎች፣ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች የግንዛቤ ፈጠራ እና አቅም ግንባታ ስልጠናዎች እንዲዘጋጁ፣ ለግንዛቤ ፈጠራ የሚያገለግሉ ሰነዶች እንዲደራጁ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣
- በፖሊሲው መሰረት ተግባርና ኃላፊነት በተሰጣቸው ተቋማት መካከል በሀገር-አቀፍ ደረጃ ዘላቂ ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር እንዲመሰረት ያደርጋል፣
    - አንድ ወጥ አተገባበር እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎችን ያከናውናል፣
    - ቅንጅታዊ አሰራሩ ተግባራዊ መደረጉን ይከታተላል፣ አስፈላጊ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በየጊዜው የአደረጃጀቱን እይታ የሚሹ ጉዳዮች ሲነሱ የጋራ ምክክር ያደርጋል፣ ምክረ-ሀሳብ ይሰጣል፣
- በፌዴራልና በክልል የሽግግር ፍትሕ ተቋማት መካከል ተገቢ ቅንጅታዊ አሰራርና ትብብር እንዲኖር ያደርጋል፣ ይከታተላል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣
- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ነፃነት፣ ገለልተኝነትና አሰራር ባከበረ መልኩ ጥቅል የክትትል ስርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

## 6.3. የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጀት

የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ የስራውን ስፋትና ባህሪ ባገናዘበ መልኩ ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችል በጀት ይኖረዋል።

- በጀቱ በመንግስት ከሚመደብ ገንዘብ፣ ከሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶችና አጋር አካላት የሚገኝ የገንዘብና የአይነት ድጋፍ፣ እንዲሁም ከሌሎች በሕግ ከሚወሰኑ ምንጮች የሚገኝ ይሆናል።
- የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በመቀናጀት - የሽግግር ፍትህ ስርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የገንዘብና የአይነት ድጋፍ ማግኘት እንዲቻል ከተለያዩ አለም-አቀፍ እና አገር-አቀፍ አጋር አካላት ጋር በቅርበት ይሰራል። እንደአግባብነቱ በገንዘብ ሚኒስቴር አንድ ቋት - አሊያም በተናጠል በየተቋማቱ ስራ ላይ የሚውል ሀብት ያሰባስባል።

የሽግግር ፍትሕ የትግበራ ምዕራፍ የፋይናንስና የግዢ አገልግሎቶች የመንግስት ፋይናንስና ግዢ ሕግን፣ የአደረጃጀቱን ልዩ ባህሪና የትግበራ ሂደቱን ውስብስብነት ታሳቢ ባደረገ መልኩ የሚፈፀም ይሆናል።

የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጀት የፍትህ ሚኒስቴርን የፋይናንስና ግዢ ክፍል  የአገልግሎት መሰረተ-ልማት የሚጠቀም ይሆናል።

የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጀት ዝርዝር ቀጥሎ በተመለከቱ የተለያዩ ንኡስ ክፍሎች ይቀርባል።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ተቋማዊ ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ[3] | ለትግበራ የሚያስፈልግ በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መመስረት | ፍትሕ ሚኒስቴር | ምዕራፍ 1:<br>ነሀሴ 15 2016 ዓ.ም) | |
| 2. | የሽግግር ፍትህ ስራዎችን | የሽግግር ፍትህ የተቋማት | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም- | |

[3] በሚቀጥሉት አስራ-አምስት ወራት የጊዜ ማዕቀፍ ላይ የሚያተኩሩት ዋና ዋና የትግበራ ስራዎች በአምስት የተለያዩ ምዕራፎች ተከፋፍለው የሚከናወኑ ይሆናል።
ምዕራፍ 1 (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ ምዕራፍ 2 (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ ምዕራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፣ ምዕራፍ አራት (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፣ እንዲሁም ምዕራፍ አምስት (ከሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ያለውን ጊዜ የሚሸፍኑ ይሆናል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በተመለከተ የጋራ ክትትል ስርዓት መዘርጋት | ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡[4] | ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 3. | መደበኛ ስብሰባዎች ማካሄድ (4) | ሴክሬታሪያት፡ | ከመስከረም እስከ ነሐሴ 2017 ዓ.ም | |
| | | | | |

## 7. በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚከናወኑ የትግበራ ስራዎች ተመጋጋቢነትና ቅደም-ተከተልን የሚመለከቱ ጉዳዮች

### 7.1. በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል ውድድር ለማስቀረት/ተመጋጋቢነት ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ተግባራት

የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ የሚፈለገውን ግብ እንዲያሳካ ይዘቱን ሁሉን-አቀፍ በሆነ መንገድ መቅረፅ ብቻ ሳይሆን - የሚተገበሩ የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስልቶች በተመጋገቡ፣ በተቀናጀና ተገቢ ቅደም-ተከተልን በሚጠብቅ አግባብ መከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

የሽግግር ፍትህ ሂደት በርካታ ተቋማትን የሚያሳትፍ እንደመሆኑ መጠን - በፍኖተ-ካርታውና በቀጣይ በሚወጡ ህጎች ላይ በትግበራ ሂደት አንዱ የሽግግር ፍትህ ስልት ከሌላው ስልት ጋር የሚኖረውን መስተጋብር እና መደጋገፍ መለየት፣ እንዲሁም ለዚህ የሚያስፈልገውን አሰራር በግልፅ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

### 7.2. የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል ጥቅል እቅድ

በሽግግር ፍትህ ስራዎች መካከል - አላባዎቹ ከሚኖራቸው አንፃራዊ ተፅእኖ ወይም ውጤት ጋር በተያያዘ የሚመሰረት የተለየ ማበላለጥ አይኖርም፡፡ በፖሊሲው ላይ በግልፅ እንደተንፀባረቀው - በዚህ ረገድ ተመራጩ አካሄድ የሽግግር ፍትህ የተለያዩ ስራዎችን በአንድ ሁሉን-አቀፍ የፖሊሲ ማዕቀፍ ማካተትና መተግበር ነው፡፡

ይሁን እንጂ ሁሉን-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ማለት የግድ ሁሉንም ተግባራት ባንድ ጊዜ ማከናወን ይገባል ማለት አይደለም፡፡ የሽግግር ፍትህ የተለያዩ አምዶች ትግበራ ቅደም-ተከተል ውሳኔ - በዋናነት መሬት ላይ ያሉ ተጨባጭ እውነታዎችን፣ የፀጥታ ሁኔታዎችን፣ የህዝብ ፍላጎቶችን፣ በተለያዩ የፖለቲካ ሀይሎች እና የፖለቲካ ምህዳሩ የሚገለፁ ፅኑ ማረጋገጫዎችን፣ የአገር የረጅም ጊዜ ጥቅሞችን/ግቦችን፣ የሀብት ዝግጅት፣ እና ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሌሎች ተግዳሮቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት ጭምር የሚከናወን ነው፡፡

ስለሆነም በዚህ ፍኖተ-ካርታ ላይ አመላካች የጊዜ ቅደም-ተከተል ቢቀመጥም - በተጨባጭ ተግባራዊ አፈፃፀሙ በዚህ መርህ/ታሳቢዎች እና በአጭር ጥናት ላይ ተመስርቶ የሚከናወን ይሆናል፡፡

በሁሉም የሽግግር ፍትህ ስልቶች ትግበራ ስራዎች መካከል ተመጋጋቢነት ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ - ከስራዎቹ ባህሪ እና ኢትዮጵያ አሁን ላይ ከምትገኝበት ውስብስብ የግጭት እና የሰብአዊ መብቶች አከባበር አውድ አንፃር አራት አንኳር ስራዎች ማለትም፡-

- ‘የህዝብ ንቅናቄ/አድቮካሲ’ ስራዎች፣
- ‘የተቋማዊ አቅም ግንባታ ቅድመ-ዝግጅት ስራዎች’፣
- ‘የወንጀል ተጠያቂነት’ እና
- ‘የእውነት ማፈላለግ/ማውጣትና ምህረት ስራ ሂደቶች’ ልዩ ትኩረት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ተግባራት ይሆናሉ፡፡

ይህ ልዩ ትኩረት ስልቶቹ በንፅፅር አገራዊ ጥቅም፣ እርቅና ዘላቂ የሰላም አጀንዳ ለማራመድና የተሻለ የዲሞክራሲ ሥርዓት ሽግግር እውን ከማድረግ አኳያ ከሚኖራቸው የገዘፈ ሚና (ብቻ) የሚመነጭ ነው፡፡

---

[4] ከዚህ በኋላ ‘ሴክሬታሪያት’ ተብሎ የሚጠራ ይሆናል፡፡

በመሆኑም 'የዘላቂ ማካካሻ' እና 'የተቋማዊ ማሻሻያ' ስራዎች በቅደም-ተከተል ደረጃ በቀጣይ የሚከናወኑ ተግባራት ይሆናሉ። ሆኖም ይህ ውሳኔ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የሚጀመሩ የማካካሻ ሥርዓት ውስን ክፍሎች አይኖሩም ማለት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል።

ከዚህ አንፃር የሽግግር ፍትሕ አላባዎች ትግበራ በተመጋገበ እና ሚዛናዊ ቅደም ተከተልን በጠበቀ አግባብ ለማሳለጥ እንዲቻል፡

- በተቋማት መካከል 'ተመጋጋቢ፣ የተቀናጀና ቅደም-ተከተልን የጠበቀ (complementary, coordinated and justifiably sequenced) የስራ ግንኙነት' እንዲኖር የሚያስችል፡
- መንግስት ከሚኖረው እይታ፣ በሂደቱ ላይ ጠንካራ የህዝብ እምነት ከመመስረት እና አጠቃላይ የፖሊሲውን ትግበራ የሰመረ ከማድረግ አንፃር አላባዎችን በአንድ ጊዜ አሊያም በተለያዩ ምእራፎች በቅደም-ተከተል ወደ ትግበራ ማስገባት የሚኖረውን ልዩ ጥቅም ወይም ጉዳት የሚያመላክት፡
- እንዲሁም አላባዎችን በአንድ ጊዜ ወይም በተለያዩ ምእራፎች ከመተግበር ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ተፅእኖ አነስተኛ ለማድረግ መወሰድ የሚኖርባቸው እርምጃዎችን ዝርዝር የሚያመላክት አንድ ገላጭ ሰነድ ከጅምሩ ይዘጋጃል።

የተለያዩ የሽግግር ፍትህ ስራዎች በቅደም-ተከተል የሚተገበሩበትና የሚደራጁበት ሁሉን-አቀፍ አሰራርና የትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ (sequenced implementation - master deck) በአባሪ 1 ላይ ተመልክቷል።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 4. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት መካከል ተመጋጋቢ፣ የተቀናጀ እና ቅደም-ተከተልን የጠበቀ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል አንድ ገላጭ ሰነድ ዝግጅት፡ | ሴክሬታሪያት | ምዕራፍ 1:<br>ነሀሴ 30 2016 ዓ.ም | |
| | | | | |

## 8. ህዝባዊ ገፅታ የማላበስ/የማንቃት እና መደበኛ የህዝብ ግንኙነት ስራዎች የሚከናወኑበት አግባብ

በሀገር መሪነትና የሕዝብ ባለቤትነት መርህ ላይ የተዋቀረ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ግንባታ ሂደት የህዝብ ተሳትፎን የሚያረጋግጥና ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍ የሚያገኝበትን አሰራር የሚቀይስ መሆን አለበት። ይህን ዓላማ ለማሳካት ፖሊሲውን እና የትግበራ ሂደቱን በተደራጀ መንገድ የማስተዋወቅና ህዝባዊነት የማላበስ ስራዎችን ማከናወን፣ እንዲሁም አጠቃላይ ሂደቱ በግልፀኝነት መርሆች የሚመራ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ህዝቡና ባለድርሻ አካላት ከሂደቱ ጋር በተያያዘ የሚከናወኑ ስራዎችን በተመለከተ በተደራጀና በቀላሉ በሚረዱት ቋንቋ ግልፅ መረጃ የሚያገኙበት አሰራር መዘርጋትም ተገቢ ይሆናል።

በመሆኑም በተቋማትና ባለድርሻዎች ቅንጅታዊ አሰራር ማዕቀፍ - ከኢትዮጵያውያን ፍላጎት፣ ተስፋና የጋራ ትልም ጋር የተንሰላሰለ ውጤታማ የሽግግር ፍትህ ስራ ለማከናወን፦

- የፖሊሲውን መሰረታዊ ሀሳቦች፣ ግቦችና የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ሚና ለህዝብ ግልፅ ማድረግ፣
- የሽግግር ፍትህ አንኳር ሰነዶችን በብዙ የአገሪቱ ቋንቋዎች እንዲተረጎሙና ተደራሽ እንዲሆኑ፣
- እንደአግባብነቱ በትግበራ ዋና ዋና ምዕራፎች የህዝብን ተሳትፎና የባለድርሻ አካላት ድጋፍና የባለቤትነት ስሜት የሚያጠናክሩ ስራዎችን (ህዝባዊ ውይይቶች፣ ስልጠናዎች ወዘተ) ማከናወን፣
- በድህረ-ገፅ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ፕሮግራሞች እና በፕሬስ ድርጅቶች አማካኝነት ማህበረሰብን የማሳወቅ ተከታታይ ሥራዎችን መስራት ያስፈልጋል።

የሽግግር ፍትህ ሂደቶችን ህዝባዊነት ከማረጋገጥ፣ ህዝብን ከማነቃቃት እና ውጤታማ የህዝብ ግንኙነት ስራዎችን ከማሳለጥ አንፃር የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 5. | የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ/ትግበራ ሂደቶችን አጠቃላይ ስእል የሚሰጥ መሰረታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በተለያዩ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፣ (1)<br>በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፣ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፣<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 6. | የህዝብ ተሳትፎ ለሽግግር ፍትህ ውጤታማነት ያለውን ሚና የሚያሳይ በህዝብ አስተያየት ላይ የተመሰረተ የቲቪ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ማስተላለፍ፣ (12) | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 7. | በሽግግር ፍትህ አላማና ግቦች ላይ የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሄር አጭር መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣<br>የፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 8. | በሽግግር ፍትህ አላማ/ግቦች ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 9. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ምዕራፍ ክልሎችና ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 10. | የእምነት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲን በመተግበር ሂደት በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ተከታታይ አገር-አቀፍ የፓናል ውይይቶችን ማካሄድ፣ (3) | ሴክሬታሪያት፣<br>የሀይማኖት ተቋማት ምክር ቤት፣<br>የክልል መስተዳድሮች፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 11. | ለፌዴራልና ክልል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ለክልል ምክር ቤት አባላት የፖሊሲውን ይዘት እና የትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፣ (14) | ሴክሬታሪያት፣<br>ከተቋማቱ ጋር በመተባበር | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 12. | በሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ለሚገኙ የዞንና የወረዳ ሀላፊዎች የፖሊሲውን ይዘት/የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፣ (28) | ሴክሬታሪያት፣<br>ከተቋማቱ ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 13. | በአዲስ አበባ/በክልል ደረጃ በሰብዓዊ መብት፣ ግጭት አፈታት፣ የሕግ የበላይነትና ፍትህ ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ (awareness, briefing) መድረኮች ማዘጋጀት፣ (10) | ሴክሬታሪያት፣<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣<br>ምዕራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 14. | ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የፖሊሲው | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 2፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ይዘትና ትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (2) | ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 15. | በሀገሪቱ ለሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበረሰብና ከፍተኛ አመራር የፖሊሲ ይዘት/ትግበራ ሂደቱን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | ሴክሬታሪያት፡<br>ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 16. | ለዳያስፖራ ማህበረሰብ ተወካዮች የፖሊሲውን ይዘትና የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (በአውሮፓ፡ አሜሪካ፡ በአረብ ሀገራት፡ ውስን የአፍሪካ አገራት) (5) | ሴክሬታሪያት፡<br>ከዳያስፖራ ኮሚሽን እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 17. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆችና ሌሎች ህጎች ላይ ህዝብ ዝርዝር አስተያየት የሚሰጥበት ከመደበኛው አሰራር የተለየ አገር-አቀፍ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፡ (ለአንድ ረቂቅ ህግ 5 አገር-አቀፍ መድረኮች) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 18. | የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱን፡ የህዝብ ምክክርና ግብአት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት፡ እና የፖሊሲውን አማርኛና እንግሊዝኛ ቅጂ በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 19. | የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን የትግርኛ፡ ኦሮምኛ፡ አፋርኛ፡ ሲዳምኛ፡ ጉራግኛ እና ሶማሊኛን ጨምሮ - ቢያንስ በአስር አገራዊ ቋንቋዎች መተርጎም፡ ቅጂውን በህትመት፡ በማህበራዊ ገጾች እና ድህረ-ገፆች ተደራሽ ማድረግ፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከየክልሎቹ ፍትህ ቢሮዎች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 20. | የሽግግር ፍትህ ሂደትን የሚመለከቱ ትምህርቶችን/መልዕክቶችን የያዙ አጫጭር ተከታታይ ዘጋቢ ቪዲዮዎችን የሚያዘጋጅ የዘርፉ ባለሙያ መቅጠር፡ ማስማራት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 21. | በስኬታማ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ያለፉ አገራት ተሞክሮን የሚያሳዩ ታሪካዊና ምስላዊ ቅንብር ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (2) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 22. | የሽግግር ፍትሕን የተለያዩ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድራማና ካርቱን አጫጭር ቪዲዮዎች ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (5) | ሴክሬታሪያት፡ | ከምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 23. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች (ተጎጂዎች፡ የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች፡ ተፈናቃዮች፡ አካል ጉዳተኞች ወዘተ) የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ልዩ ሁኔታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማደራጀት፣ ማሰራጨት፣ (1) | | | |
| 24. | ለሚዲያ ተቋማት የሚሰጡ መረጃዎች አይነት፣ መረጃ ስለሚሰጥበት ጊዜ/አግባብ፣ የመረጃ/የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት፣ መረጃ ስለሚሰጠው አካልና ከሚዲያ ተቋማት ጋር የሚኖር ግንኙነትን የሚገዛ ሁሉን-አቀፍ የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ ስራ ላይ ማዋል፤ (1) | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 25. | ከሚዲያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በመደበኛነት ምላሽ የሚሰጥ ባለሙያ ማዘጋጀት፣ አከራካሪና የብዙሀኑ ሚዲያ ጥያቄ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ ወጥ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ማሳወቅ፣ | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 26. | የሚዲያ ተቋማትና ባለሙያዎች ፖሊሲውንና የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በተመለከተ የሚያዘጋጇቸው ዘገባዎች በሙሉ እውቀት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ለማድረግ - ለሚዲያ ተቋማት አመራሮች፣ ለዜና እና ፕሮዳክሽን ክፍል ዋና ኤዲተሮች፣ ሪፖርተሮች፣ የመንግስት የህዝብ ግንኙነት አመራሮች፣ ለማህበረሰብ-ዐቀፍ ሬዲዮ ተወካዮችና ለተመዘገቡ ዩቲዩበሮች ተከታታይ ይዘት-ተኮር ስልጠናዎችን፣ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ መስጠት፣ (6) | ሴክሬታሪያት፣ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 27. | የሚዲያ ተቋማት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ተከታታይነት ያላቸው የራሳቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች እንዲቀርፁ ማድረግ፣<br>የተመረጡ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ (በሳምንት አንድ፣ በአመት 52) | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣<br>የሚዲያ ካውንስል፣ | ከምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 28. | በፖሊሲ ትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ ስራዎችን በምስል (ስፖት) ማቀናበር፣ ለሚዲያ ተቋማት መላክ፣ በሽግግር ፍትህ፣ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፣ (26) | ሴክሬታሪያት፣ | ከምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 29. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፣<br>ለሚዲያ ተቋማት መላክ፣ በሽግግር ፍትህና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆችና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፣ (12)<br>ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፈረንስ ማካሄድ (4) | ሴክሬታሪያት፣ | ከምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 30. | በሁሉም የሽግግር ፍትህ ሂደት የሰነድና ዜና ዝግጅቶች ላይ የሚሰፍር ቋሚ ታግላይን | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ማዘጋጀት፡ ጥቅም ላይ ማዋል፡ (“የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት በሀገር መሪነትና ህዝብ ባለቤትነት እውን ይሆናል”) (1) | | | |
| 31. | በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ለሚዲያዎች በሚሰጥ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የሽግግር ፍትሕ ጉዳይ መደበኛ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፡ ከአመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፡ ውሳኔ ማሳለፍ፡ | ሴክሬታሪያት፡ የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 32. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፡ ዓለም-አቀፍ ተቋማትና የልማት አጋሮች መደበኛ የመረጃ ልውውጥ (briefing) መድረኮችን ማዘጋጀት፡ (4) | ሴክሬታሪያት፡ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| | | | | |

## 9. ሕጎች የማውጣት ስራ

በኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓትን በተሟላ መንገድ ተግባራዊ የማድረግ ስራ የተለያዩ ህጎች ማውጣትን ይጠይቃል። በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ላይ ግልፅ አቅጣጫ ከተሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ አዲስ የይዘት ሕግ ማዕቀፍ (substantive law) ዝግጅትን የሚመለከት ሲሆን፡ ሁለተኛው ወደፊት የሚደራጁ ተቋማት የማቋቋሚያ ህጎች ማውጣትን የሚመለከት ነው።

ስለሆነም በፖሊሲ ሰነዱ የተመላከቱ ጉዳዮችን ለማስፈጸም የሚያስችሉ የህግ ማእቀፎችን ምንነት በፍኖተ-ካርታው ላይ በግልጽ እንዲዘረዘሩ ተደርጓል።

### 9.1. አዲስ የሕግ ማዕቀፍ የሚወጣለት ጉዳይ እና የረቂቅ ዝግጅት

አዲስ የይዘት ሕግ ማዕቀፍ የሚወጣለት ጉዳይን በተመለከተ በፖሊሲው ላይ የተቀመጠው ተቀዳሚ ስራ ‘የዓለም-አቀፍ ወንጀሎች አዋጅ’ ዝግጅትን የሚመለከት ነው። ይህ የስራ ሂደት በዋናነት፥

- በሀገሪቱ የወንጀል ሕግ ውስጥ ያልተካተቱ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን (በተለይም በሰብዓዊነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፡ ከፍርድ ውጭ ሰው መግደል፡ ሰው ማሰቃየት፡ ሰው መሰወር፡ ከባድ ጾታዊ ጥቃት እና የተወሰኑ የጦር ወንጀል) ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸው ዓለም-አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማጣጣም አዲስ የሕግ ማዕቀፍ መቅረጽን፡
- እንዲሁም ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በማካተት የሚወጣው ሕግ መሰረት የዓለም-አቀፍ የልማድ ሕግ (customary international law) እንደመሆኑ መጠን የተፈፃሚነት ወሰኑ ሕጉ ከሚጸናበት ቀን በፊት የተፈጸሙ ዓለም-አቀፍ ወንጀሎችን በሚያቅፍ አግባብ እንዲመሰረት የሚፈቅድ የሕግ መርህ መመስረትን የሚያካትት ነው።

በፍኖተ-ካርታው ላይ የሕግ ማርቀቅ ስራ ለማጠናቀቅ የተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍ ለሕጉ መነሻ የሚሆን የዳሰሳ ጥናት ዝግጅት የሚወስደውን ጊዜ፡ በረቂቅ ሕጉ ላይ የሚደረጉ ምክክሮችን፡ ረቂቁን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ልኮ ለማስፀደቅ የሚወስደውን ጊዜ፡ እና ሂደቱ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚቀይበትን ጊዜ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 33. | የአለም-አቀፍ ወንጀሎች አዋጅ፡<br>- የረቂቅ ዝግጅት፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት፡<br>- የረቂቅ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፡<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br><br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 9.2. የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ዝግጅት

የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደትን ውጤታማነት ከሚወስኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ እና ዋናው በፖሊሲው ላይ የተቀመጡ ዓላባዎችን የሚተገብሩ ነጻ እና ገለልተኛ ተቋማት ማቋቋም ነው። በፖሊሲው እሳቤ መሰረት እነዚህን ተቋማት - ተገቢ ስልጣን፣ ሀላፊነት፣ የአሰራር ሥርዓትና ተያያዥ ገዢ መርሆችን ባካተተ አግባብ እንዲቋቋሙ ማድረግ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው።

በዚህ ረገድ የሚዘጋጁ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች - በውስጣቸው የተለያዩ ርእሰ-ጉዳዮችን ሁሉን-አቀፍ በሆነ መልኩ በመያዝ የሚወጡ ይሆናል።

ስለሆነም ፖሊሲውን በሙሉ ሀይል የሚተገብሩ ተቋማትን ከማደራጀት አንፃር የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት የሚከተሉት ናቸው።

### ሀ) የወንጀል ምርመራና ክስ ስራዎች፡

የወንጀል ምርመራና ክስ ስራ የሚያከናውን የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅት በውስጡ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በሚያካትት አግባብ እንዲወጣ ይደረጋል።

- የወንጀል ተጠያቂነት የስረ-ነገር ወሰን የሚያርፍባቸው ጉልህ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች/ከባድ ወንጀሎችን ሰፋ ካለ ማእዘን በማየት ለመለየት የሚያስችል ግልፅ መስፈርት ዝግጅት፡
- የወንጀል ተጠያቂነትን የግል ወሰን (personal jursidiction) በተመለከተ በሰብአዊ መብት ጥሰት/ከባድ ወንጀል አፈፃፀም ከፍተኛ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች የሚለዩበት ግልጽ የሕግ ሥርዓት ማስቀመጥ፡
- የወንጀል ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ልዩ የምርመራና ክስ ስርዓት ማቋቋም፥ የወንጀል ምርመራ እና ክስ ስራ በተሟላ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችል፡ በሽግግር ፍትህ ሂደት የሚታዩ ወንጀሎችን ልዩ ባህሪ መሰረት ያደረገ የህግ አሰራር ማቆም (በሕገ-መንግስቱ፡ በወንጀል ሕጉ እና በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ላይ ከምርመራና ክስ ጋር በተያያዘ የተቀመጡ መርሆዎች እና ድንጋጌዎችን የሚያጠናክር)፡
- በክስና ምርመራ ሂደት የሚተገበሩ የሥነ-ሥርዓት እንዲሁም የማስረጃ ህጎች ጾታዊ ጥቃት የፈጸሙ አጥፊዎችን ተጠያቂነት ማረጋገጥ በሚያስችሉ መልኩ መመስረት፡
- በፖሊሲው የተካተቱ ወንጀሎችን በተመለከተ የወንጀል ሙሉ ተጠያቂነት ለማረጋገጥ እንዲቻል በህገ-መንግስቱ የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ያለመከሰስ መብት ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የሚያስችል መርህ መመስረት፡

- በሀገር ውስጥ የማይገኙ ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ያላቸው አጥፊዎች ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሚገኙበት አገር ተላልፈው እንዲሰጡ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ አሰራር ማቀም፣
- የማበረታቻ ድጋፍ ወይም ሽልማት የሚሰጥበት ሥርዓት፣ በመደበኛ ምርመራ ሊደረስበት የማይችል ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ አጥፊ ለጠቀመ ወይም ማስረጃ ላቀረበ ሰው የሚሰጥ የማበረታቻ ድጋፍ/ሽልማት አሰራር በህግ ማቀም፣
- ከፍተኛ ደረጃ የወንጀል ተሳትፎ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ምስክርነት የሚሰጡ ሰዎች ስለሚሰጣቸው የደህንነት ጥበቃና የስነልቦና አገልግሎት ድጋፍ ሥርዓትን የሚያደራጅ የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት፣

## ለ) የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ፣ የምህረት እና ማካካሻ ስራዎች፣

- የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ የእርቅ፣ የምህረትና ማካካሻ ተግባራትን የሚያከናውን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣
- እውነት የማፈላለግ/ይፋ ማውጣት እና የእርቅ ስራዎች ስረ-ነገር ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ጉልህ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች እና ሂደቱ የሚሸፍናቸው አጥፊዎች ወሰን በሕግ መደንገግ፣
- ምህረት በቅድመ-ሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የሚሰጥበትን ዝርዝር አግባብ፣ እንዲሁም ምህረት የማይሰጥባቸው የወንጀል አይነቶች/ተሳትፎዎችን በሕግ መመስረት፣
- የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም/ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት የሕግ ማዕቀፍ መመስረት፣

## ሐ) የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት

- ክሶችን የመስማትና ውሳኔ የመስጠት ተግባራትን የሚያከናውነው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ልዩ ችሎት ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅት፣
- ችሎቶቹ የሚኖራቸው ጉልህ ጥሰቶችን/ወንጀሎችን የማየት የመጀመሪያ፣ የይግባኝ እና የሰበር ዳኝነት ስልጣን መመስረት፣
- የዳኞች መለየት/ማጥራት፣ ማግለል እና ከህላፊነት አነሳስ የሚመለከቱ ጉዳዮችን መደንገግ፣
- የልዩ ሬጂስትራር ፅህፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች፣ እና የጉዳተኞች ድጋፍ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት አደረጃጀት ማቀም፣

## መ) የሕግና ተቋማዊ ማሻሻያ ስራ

- የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎችን የሚያከናውን ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣

**የሽግግር ፍትህ ተቋማት የማቋቋም ስራን በተመለከተ** በፍኖተ-ካርታው ላይ የተቀመጠው የጊዜ ማዕቀፍ - የየተቋማቱ ማቋቋሚያ ረቂቅ ሕጎች ለማዘጋጀት የሚወሰደውን ጊዜ፣ በረቂቅ ህጎቹ ላይ የሚካሄዱ የህዝብ ምክክሮች፣ ረቂቆችን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ልኮ ለስማፀደቅ የሚወሰደውን ጊዜ፣ እና የተቋማቱን ፅህፈት ቤትና የሰው ኃይል ለማደራጀት የሚያስፈልገውን ጊዜ ታሳቢ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 34. | የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋሚያ ሕግ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት ስራዎች፣<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን ነጻና | ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣<br>ምዕራፍ 2፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ገለልተኛ አድርጎ ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፣ የሃላፊዎች አሿሿም፣ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የዐቃብያነ ሕግና መርማሪዎች አሿሿም እና አነሳስ፣ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የስራ ዘመን፣ የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ስልጣንና ተግባር፣ የበጀት ነፃነት፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር፣ እና በስራ ላይ ያሉ ህጎች ተፈጻሚነት ላይ ያተኮረ)፣<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን አደረጃጀት፣ ስልጣን፣ ተግባር የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ማዘጋጀት፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብር አካልን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል የማደራጀት ስራ፣ | የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 35. | የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረትና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣<br>- የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ እርቅ፣ ምህረትና ማካካሻ ተግባራትን ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን፣ (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፣ የሃላፊዎች አሿሿም፣ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የኮሚሽነሮች አሿሿም/አነሳስ፣ የስራ ዘመን፣ የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፣ የበጀት ነፃነት፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት/ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ያተኮረ)፣<br>- የኮሚሽኑን ስልጣን፣ ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣ | ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም፣ ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት ሕግ ማእቀፍ ማካተት፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤትና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፣ | | | |
| 36. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣<br>- ነጻና ገለልተኛ ችሎት ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት የልዩ ችሎቱ አደረጃጀት፣ ልዩ ችሎቱ የሚያያቸው ጉዳዮች አይነት ዝርዝር፣ ዳኛ ሆኖ ለመሾም ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ ዳኞችን በተመለከተ ህዝብና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እና አስተያየት የሚሰጡበት/የልየታ እና ማጥራት ሥርዓት፣ የዳኞች ስብጥር፣ በልዩ ችሎቱ በአማካሪነት እና በአሰልጣኝነት የሚሰሩ ባለሙያዎች፣ የልዩ ችሎቱ ሬጂስትራር፣ የተጎጂዎች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ ዳኞች የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሥርዓት ላይ የሚያተኩር)፣<br>- የልዩ ችሎቱን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣<br>ከሴክሬታሪያት፣<br>ፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 37. | የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና አደረጃጀት፡<br>- የልየታ፣ ማጥራትና ማሻሻያ ስራዎችን ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነትና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ ጥናት/የአውድ ትንታኔ ማከናወን፡<br>- የልየታ፣ ማጥራትና ማሻሻያ ስርዓትን የሚመራ፣ የኮሚሽኑን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፣ የጸደቀውን ሕግ ማስተዋወቅ፡<br>- አዋጁን የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤትና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 10. የሽግግር ፍትህ ተቋማት አቅም ግንባታ ስራ

ለሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ትግበራ የሚቋቋሙ ተቋማትን በተመለከተ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በጥንቃቄ ማቀድና መተግበር ያስፈልጋል። የአቅም ግንባታ ስራዎቹ በአጭርና በረጅም ጊዜ እቅድ ማእቀፍ የሚከናወኑ ይሆናል። በዋናነትም ስራዎቹ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 38. | አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ፖሊሲውን በሙሉ አቅማቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚከተሉት መሰረታዊ የአቅም ግንባታ ስዎች ይከናወናሉ፡<br>- አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት አመራሮች በፖሊሲውና ትግበራ ሂደቶች፣ በተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ይዘት፣ በሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፡ (4)<br>- ተቋማቱ ባለሙያዎች ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፡ (4)<br>- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በቴክኒክ ሊደግፉ የሚችሉ የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በዝርዝር መለየት፡ የባለድርሻ አካላት ልየታ (Stakeholdes Mapping) ማዘጋጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልማት አጋሮችና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ ዎርክሾፕ ማዘጋጀት፡ (1) | | | |
| 39. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት በተለይ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ዝርዝር ስራዎች ይከናወናሉ፥<br>- የተቋሙ አመራሮች፡ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በዓለም-አቀፍ ወንጀሎች የምርመራና ክስ ቴክኒካዊ አሰራሮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው አማካሪዎች መቅጠር፡ (2) የአማካሪዎች ምልመላ/ሚና ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1)<br>- በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ፡ በዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ቴክኒካዊ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት/ባለሙያዎችን መለየት፡ ስልጠናዎች መስጠት፡ (4)<br>- የወንጀል ምርመራና ክስ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል ምርመራ፡ ክስና ማስረጃ አስተዳደር ስርዓት (Case Management System) ማበልጸግ፡ (1)<br>- ተጎጂ-ተኮር የምርመራና ክስ አሰራርን በተመለከተ የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፡ (1)<br>- የተቋሙ አመራርና የተመረጡ አቃብያኔ ህጎች በወንጀል ምርመራና ክስ ስራ ሂደት ስኬታማ ታሪክ ባላቸው የአፍሪካና ሌሎች አገራት የስራ ጉብኝት/የልምድ ልውውጥ መርሀ-ግብሮችን ማመቻቸት፡ (3)<br>- የሙብት ጥሰት ሰለባዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ባለበት ሆኖ የወንጀል ድርጊት ጥቆማና ማስረጃ የሚያቀርብበት ነጻ የስልክ ጥሪ ማዕከል፡ ድህረ-ገፅ ማደራጀት፡ (1)<br>- የተቋሙን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎች፡ የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ-ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br><br>የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 40. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፦<br>- የፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶች፡ የችሎት ሰብሳቢዎች፡ ዳኞች፡ ሬጂስትራሮች፡ ተከላካይ ጠበቆችና የተጎጂዎች ድጋፍ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ባለሙያዎችን በዓለም አቀፍ ወንጀሎች የክስና ክርክር መስማት፡ ችሎት አመራር፡ ውሳኔ አሰጣጥና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፡<br><br>ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ያላቸው ባለሙያዎች መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) ቅጥር ማካሄድ፡ (2)<br>- በሽግግር ፍትሕ ሂደት የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ፥ ክስና ክርክር፡ የችሎት አመራር፡ ውሳኔ አሰጣጥ፡ ተጎጂ-ተኮር የፍርድ ሂደትና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡ (3)<br>- የችሎት ፕሬዝደንቶች፡ የችሎት ሰብሳቢዎች እና የተመረጡ ዳኞች በስኬት በሚጠቀሱ የአፍሪካና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ በሽግግር ፍትሕ የወንጀል ክስና ክርክር ሂደት፡ የችሎት አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ላይ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶችና (እንደአስፈላጊነቱ) በየክልሎች የሚደራጁ ምድብ ችሎቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት እንዲደገፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ግብቶችን ማሟላት፡ ለዚህ የሚያስፈልግ የተፈላጊ መሰረተ-ልማት ቴክኒካል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1)<br>- የችሎቱን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችን፡ የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1)<br>- የተቋሙን የስራ ስፋትና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፡ የሰው ኃይልና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፡ | | | |
| 41. | የእውነት ማፈላለግ፡ ምህረትና ማካካሻ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በጉልህ አለም-አቀፍ ወንጀሎች ምርመራና ክስ፡ በአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች፡ የእውነት ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ሥርዓት ፡ በምህረትና ይቅርታ አስተዳደር እና ተመራጭ የማካካሻ ስራዎች አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) ቅጥር ማካሄድ፡ (2)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና ማዘጋጀት፡ (5)<br>- ኮምሽነሮችና ውስን የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬት በሚጠቀሱ የአፍሪካ ወይም ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት ወይም ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3) | ኮሚሽን፡<br><br>ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር የተያያዙ የታሪክ መዝገቦችን፡ የተጎጂዎች ምስክርነት ቃልና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እና ለማቆየት የሚያስችል የኮሚሽን ፊዚካል አርካይብ እንዲደራጅ ቴክኒካል መዘርዝር ማውጣት፡ (1) መሰረተ-ልማቱን እና ሙዝየም ማደራጀት፡ (1)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችና የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ቨርችዋል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1) | | | |
| 42. | የተቋማዊ ማሻሻያ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚከናወኑ ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎች ምንነት፡ አስፈላጊነት እና ዝርዝር አካሄድ ላይ ተቋሙንና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) ቅጥር ማካሄድ፡ (1)<br>- ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና ማዘጋጀት፡ (5)<br>- ኮምሽነሮችና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችንና የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ቨርቷዋል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1) | ተቋም/ኮሚሽን፡<br><br>ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 11. በሽግግር ፍትህ ትግበራ የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ለመለየት/ለማሳለጥ የሚከናወኑ ዝርዝር ስራዎች

### 11.1. መግቢያ

የሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሊያሳካው ከሚሻው ዓላማ አንፃር - በሀገር-አቀፍ ደረጃ የሚሳለጥ አንድ ወጥ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ትግበራ ሊኖር ይገባል። እንዲያም ሆኖ የሽግግር ፍትህ ስራ እንዲፈታቸው ከሚታሰቡ ጉዳዮች ይዘት፡ ብዛት፡ አካባቢያዊ ስርጭትና ውስብስብነት አንፃር ክልሎች ግልፅ ሀላፊነቶችን በመሸከም በትግበራ ምዕራፎች እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው።

በመሆኑም በቀጣይ ወራት - የሽግግር ፍትህ ተቋማትን ለመመስረት የሚወጡ ህጎች የሚያስቀምጡት ዝርዝር አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ - ክልሎች በአገራዊና አካባቢያዊ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ አውድ የሚኖራቸውን ሀላፊነት በቅልጥፍና እና ውጤታማነት እንዲወጡ ከማስቻል አንፃር የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ።

### 11.2. ክልሎች በሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ የሚኖራቸው ሀላፊነት

በፌዴራል የሽግግር ፍትህ ተቋማት የስረ-ነገር ስልጣን ማዕቀፍ ስር በሚወድቁ ጉዳዮች ማዕቀፍ፡

- ክልሎች ለፌዴራል ተቋማት የሚሰጡት ድጋፍና ትብብር ይዘትን የሚያመላክት፡[5]
- እንዲሁም ከአገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ መሰረታዊ መርሆች ጋር በተናበበ አግባብ - በክልሎች ሙሉ ባለቤትነት፡ ሀላፊነት - ገለልተኛ እና ፍትሀዊ አሰራር በመዘርጋት የሚከናወኑ ክልል-አቀፍ የእውነት ማፈላለግ፡ የእርቅና ማካካሻ የሽግግር ፍትህ ስራዎችን ዝርዝር የሚያመላክት ቴክኒካል ሰነድ ይዘጋጃል።

ለዚህ አላማ - ክልሎችና የአገራዊው የሽግግር ፍትህ ስራዎች ቅንጅታዊ አመራር መድረክ በጋራ በመሆን የግንኙነት እና አሰራር ሥርዓት ይቀርፃሉ።

ሁሉን-አቀፍ በሆነ አገራዊ የማካካሻ ሥርዓት ማዕቀፍ ክልሎች የሚተገብሯቸው የማካካሻ ስራዎች (ካሳ፡ ማገገሚያ፡ ወደ ነበሩበት መመለስ፡ እርካታ፡[6] እና ያለመድገም ዋስትና) አይነትን፡ ሂደት፡ አተገባበርና አመላካች የጊዜ ሰሌዳን የሚመራ ማንዋል በጋራ ይዘጋጃል።

በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የሕግ ማዕቀፎችና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፡ ለማጥራትና ለመለወጥ የሚረዳ ስትራቴጂ ይዘጋጃል፡ ተቋማትን የመገንባት ስራ ይከናወናል።

እንዲሁም ክልሎች - ከአገራዊ የሽግግር ፍትህ ቅንጅታዊ አመራር አደረጃጀት እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመቀናጀት - በታችኛው መዋቅር የሚገኝ ህዝብ የሽግግር ፍትሕ ሂደቱን በተመለከተ ተገቢ ግንዛቤና አመኔታ እንዲኖረው ለማድረግ፡ ተሳታፊነቱን ለማረጋገጥ፡ የህዝቦችን ሰላም ለማጎልበት እና በጉዳዩ ላይ የአላማ አንድነት ለማጠናከር የሚያስችሉ ተከታታይና የተደራጁ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮች ያዘጋጃሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 43. | በሽግግር ፍትህ አተገባበር የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ዝርዝር የሚያስቀምጥ ሁሉን-አቀፍ መሪ ሰነድ (Comprehensive Guiding Document) ማዘጋጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br><br>ከክልሎች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 44. | በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የሕግ ማዕቀፎችና ቅድሚያ የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፡ ለማጥራት እና ለመለወጥ የሚረዳ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት፡ የተቋማዊ ሪፎርም መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፡ ትግበራ መጀመር፡ | የክልል ፍትህ ቢሮዎች፡ መስተዳድሮች፡ | ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 12. የባህላዊ ፍትህ ስርዓቶች ሚና

[5] የክልሎች ተሳትፎ ዝርዝርን በተመለከተ - የሚዘረጋው ሥርዓት ትኩረት በሚከተሉት ተግባራት ላይ ሊሆን ይችላል፥- ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓቶችን መለየት/መምረጥ፡ ተጎጂዎችን መለየት፡ የማካካሻ ስራን በገንዘብ መደገፍ፡ ተጎጂዎችን መልሶ ማቋቋም፡ የጥሰት ታሪክን ለማከም የሚረዱ ማስታወሻዎችን ማዘጋጀት፡ ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ መሳካት የሚፈለጉ ማስረጃዎችን ማቅረብ፡ የውይይት ጊዜና ቦታዎች ማዘጋጀት፡ ሎጂስቲክስን ማሳለጥ፡ ጥፋተኞችን ሪፖርት ማድረግ/ለፍርድ ማቅረብ፡ የሚያስተዳድሩት ህዝብ በሽግግር ፍትሕ ሂደቱ ላይ አመኔታ እንዲኖረው የግንዛቤ መድረኮችን ማዘጋጀት፡ የህዝቦች አብሮነት እና ግንኙነት የሚያጠናክሩ ስራዎችን መስራት፡ የክልሉን ህዝብ ተሳታፊነት ማረጋገጥ፡ ለተቋማዊ ሪፎርም ዝግጁ መሆን፡ የጸጥታ እገዛ ማድረግ።

[6] የትግበራ ስራዎቹ የጥሰቶችን ሙሉ ሀቅ ማፈላለግ/ይፋ ማውጣት፡ እንደ መንግስት ለተፈጸሙ በደሎች በተለያየ መንገድ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ (ለምሳሌ ለተለዩ ተጎጂዎች የይቅርታ ደብዳቤ መጻፍ)፡ የመታሰቢያ/ማስታወሻ ክንዋኔዎች ማዘጋጀት/ስያሜዎች መስጠት ያካትታል።

ኢትዮጵያ በርካታ ባህላዊና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ያሏቸው ማህረሰቦች አገር እንደመሆኗ መጠን - እነዚህ ሥርዓቶች በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ሚና እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል።

ባህላዊና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በአገራዊና አካባቢያዊ የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ አውድ የሚኖራቸውን ሀላፊነት እንዲወጡ ከማድረግ አንፃር የሚከተሉት ዝርዝር ተግባራት ይከናወናሉ።

ክልሎች በአገር-አቀፍ የሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶችን በሚቀመጡ ግልፅ መመዘኛዎች መሰረት ይለያሉ፣ ያሳውቃሉ፣ ለዚህ የሚሆን ዝርዝር ቴክኒካል ማንዋል ይዘጋጃል። ሰነዱ፦

- ባህላዊና ሃይማኖታዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎች በሽግግር ፍትህ ሂደት የፌዴራል መንግስትን ሆነ ክልሎችን በማገዝና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመቀናጀት በእውነት ማፈላለግ፣ በእርቅ፣ ተጠያቂዎች ለፍትህ እንዲቀርቡ በመርዳት፣ እና በማካካሻ ስራዎች የሚኖራቸውን ሚና፣
- እንዲሁም ተቋማቱ የሚለዩበት መመዘኛ፣ ሀላፊነትና እውቅና የሚያገኙበትን አግባብ፣ ገለልተኛነታቸውን፣ ነጻነታቸውንና ተዓማኒነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተጠባቂ አነስተኛ ማሻሻያዎችን፣ እና
- ጉዳዮችን ተጎጂ-ተኮር በሆነ አግባብ ማከናወን እንዲችሉ የሚያግዙ የአደረጃጀት እና ይዘት ስልጠና ስራዎች የሚከናወኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ይሆናል።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 45. | በሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መለያ እና ማሳወቂያ አሰራር፣ የሚኖራቸው ሀላፊነት፣ እና ስራቸውን የሚያከናውኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ማንዋል ዝግጅት፣ (1) | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሴክሬታሪያቱ ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 46. | የተመረጡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማትን አቅም የመገንባት ስራ፣ (2 ዙሮች) | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሴክሬታሪያቱ ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምዕራፍ 4፣ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፣ | |

## 13. ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች በትግበራ ሂደት የሚኖራቸውን ሚና ለመለየት/ለማስፈፀም የሚከናወኑ ተግባራት

### 13.1. አጠቃላይ ስራዎች

የሽግግር ፍትህ የትግበራ ሂደት የከባድ ሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባዎችን ጨምሮ ልዩ ትኩረት ለሚሹ እና ለጉዳት ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይም ለሴቶች፣ ለህጻናት፣ ለወጣቶች፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለአረጋውያን እና ለሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ልዩ ፍላጎት እና ጥቅም ትኩረት በሚሰጥ አግባብ ሊከናወን ይገባል።

በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የተጋላጭ ህብረተሰብ ክፍሎችን ተሳትፎ እና ጥበቃ ከማረጋገጥ አንፃር የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 47. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ዝርዝር ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ መተግበር፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br><br>ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣<br><br>የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ እና አጋሮች ጋር በመቀናጀት፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 48. | የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ስራዎች የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎችን ድምፅ እና ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የክትትል ሥርዓት (Monitoring Mechanism) ማዘጋጀት፡ መደበኛ የክትትል ስራዎች ማከናወን (2)፡ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅት፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 49. | የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል የስራ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ፡ | ሴክሬታሪያት፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡<br><br>ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## 13.2. ለፆታ ጥቃት ሰለባዎች ልዩ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት የሚተገበሩ ተጨማሪ እርምጃዎች

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 50. | የወንጀል ተጠያቂነት ስራ ሂደቶች ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ምቹ፡ አሳታፊና ደህንነትን ያስጠበቀ ማድረግ፡<br>ይህን የሚያግዝ ራሱን የቻለ ንኡስ መዋቅር ማደራጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br><br>ከኮሚሽኖች እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 51. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፡ የምክር እና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ አደረጃጀት/ሥርዓት እንዲመሰረት ማድረግ፡<br>የፆታ ጥቃት ሰለባ አገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን (አንድ ማእከሎች፡ ማገገሚያ ተቋማት) ማጠናከር፡<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፡ መተግበር፡ | ሴክሬታሪያት፡<br><br>ከኮሚሽኖች፡<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 52. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፡ ምክርና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ጊዜያዊ አደረጃጀት መመስረት፡ ማጠናከር፡ ስራዎችን መተግበር፡ | ሴክሬታሪያት፡<br><br>ከኮሚሽኖች፡<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 53. | በሽግግር ፍትህ ረጅም ጊዜ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ኢኮኖሚያዊ (ራስ-አገዝ) አገልግሎት የሚቀርብበት አደረጃጀት መመስረት፡ ማጠናከር፡<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፡ መተግበር፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከኮሚሽኖች፡<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፡ | ከምዕራፍ 5፡ (ሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |

## 14. የሽግግር ፍትህ ትግበራ መረጃዎች የሚያዙበት፡ የሚደራጁበት እና ተደራሽ የሚሆኑበት የመረጃ ቋት ስርዓት

የሽግግር ፍትህ አገራዊ መርሀ-ግብሩን የሚመለከቱ መረጃዎች በአንድ ማእከል የሚደራጁበትና ለህዝብ ተደራሽ የሚደረጉበትን የዘላቂ መሰረተ-ልማት ዝርጋታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉት ዝርዝር ስራዎች ይከናወናሉ።

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ | በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 54. | የመረጃ መሰረተ-ልማት ግንባታ<br>ሀ) ድህረ-ገፅ እና ማህበራዊ ሚዲያ፡<br>- የሽግግር ፍትሕ አገር-አቀፍ ስራዎችን ሂደት፡ ረቂቆች፡ ቃለ-ጉባዔዎች፡ የምክክር ሂደቱ የምስልና የድምጽ ሪከርዶች፡ ዋና ዋና ሰነዶች፡ ዘገባዎችና ወቅታዊ ሪፖርቶችን የሚይዝ ድህረ-ገፅ ስራ ማጠናቀቅ፡ ከአልሚው መረከብ፡<br>- ለዚሁ ዓላማ ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር ኪራይ መፈጸም፡<br>- ድህረ-ገፁን እና ሌሎች ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የሚከፈቱ የመረጃ ማከማቻ እና ማጋሪያ ዘዴዎችን የሚያስተዳድር፡ በየወቅቱ በአዳዲስ መረጃዎች የሚያደራጅ የሚከታተል፡ ከፍተኛ ብቃት ያለው ቋሚ የዘርፍ ባለሙያ መቅጠር፡ መመደብ፡<br>- ተመሳሳይ መረጃዎችን በተመጠነ አግባብ በፌስቡክ እና ትዊተር ገፆች ላይ ማሰፈር፡<br>- የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና መረጃዎችን በማእከላዊነት የሚይዝ ትልቅ አቅም ያለው መጠባበቂያ የውጭ ቋት (external database/ backup drive) ማዘጋጀት፡<br>ለ) አርካይቭ<br>- የሽግግር ፍትህ ስራ ሂደቶችን የሚመለከቱ የተመረጡ በወረቀት የተዘጋጁ መሰረታዊ ሰነዶች ሚስጥራዊነትና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ማእከላዊ የአርካይቭ ሥርዓት ማደራጀት፡ ለዚህ የሚያገለግሉ ፅህፈት-ቤትና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፡<br>ሐ) ሙዚየም<br>- የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ዝግጅት ሂደት እና የትግበራ ስራዎችን በተሟላ መልኩ የሚገልፅ በየጊዜውም እየተሟላ የሚሄድ ማሳያ (ሙዝየም) ሴክሬታሪያቱ በሚገኝበት የፍትሕ ሚኒስቴር ህንፃ ውስጥ እንዲደራጅ ማድረግ፡ | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| | | | | |

## አባሪ 1: የሽግግር ፍትህ ስራዎች ትግበራ ቅደም-ተከተል አጠቃላይ እቅድ

## (Sequenced Implementation – Master-Deck)

| | የሚከናወኑ ተግባራት | የማስተባበር ተቋማዊ ኃላፊነት | የሚከናወንበት ጊዜ[7] | ለትግበራ የሚያስፈልግ በጀት (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ መመስረት | ፍትሕ ሚኒስቴር | ምዕራፍ 1: (ሐምሌ 2016 ዓ.ም) | |
| 2. | የሽግግር ፍትህ ስራዎችን በተመለከተ የጋራ ክትትል ስርዓት መዘርጋት | የሽግግር ፍትህ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡[8] | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም- ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 3. | መደበኛ ስብሰባዎች ማካሄድ (4) | ሴክሬታሪያት፡ | ከመስከረም እስከ ነሐሴ 2017 ዓ.ም | |
| 4. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት መካከል ተመጋጋቢ፣ የተቀናጀ እና ቅደም-ተከተልን የጠበቀ የስራ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል አንድ ገላጭ ሰነድ ዝግጅት፡ | ሴክሬታሪያት | ምዕራፍ 1: ነሀሴ 15 2016 ዓ.ም | |
| 5. | የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ/ትግበራ ሂደቶችን አጠቃላይ ስእል የሚሰጥ መሰረታዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰነድ በተለያዩ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡ (1)<br>በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | የሽግግር ፍትህ ቋሚ የተቋማት ቅንጅታዊ አመራር መድረክ ሴክሬታሪያት፡<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም- ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 6. | የህዝብ ተሳትፎ ለሽግግር ፍትህ ውጤታማነት ያለውን ሚና የሚያሳይ በህዝብ አስተያየት ላይ የተመሰረተ የቲቪ ፕሮግራም ማዘጋጀት፡ ማስተላለፍ፡ (12) | ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 7. | በሽግግር ፍትህ አላማና ግቦች ላይ የሀገሪቱ ርዕሰ-ብሄር አጭር መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የፕሬዚደንት ጽህፈት ቤት፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 8. | በሽግግር ፍትህ አላማ/ግቦች ላይ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ መልዕክት ተቀርጾ በዋና ዋና ቋንቋዎች በሁሉም ሚዲያዎች እንዲተላለፍ ማድረግ፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባኤ ጽ/ቤት፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 9. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ምዕራፍ ክልሎችና ባህላዊ የፍትህ ስርዓቶች የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፡ ማሰራጨት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |

---

[7] በሚቀጥሉት አስራ-አምስት ወራት የጊዜ ማዕቀፍ ላይ የሚያተኩሩት ዋና ዋና የትግበራ ስራዎች በአምስት የተለያዩ ምዕራፎች ተከፋፍለው የሚከናወኑ ይሆናል።
ምዕራፍ 1 (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ ምዕራፍ 2 (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ ምዕራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ ምዕራፍ አራት (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ እንዲሁም ምዕራፍ አምስት (ከሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ያለውን ጊዜ የሚሸፍኑ ይሆናል።

[8] ከዚህ በኋላ 'ሴክሬታሪያት' ተብሎ የሚጠራ ይሆናል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 10. | የእምነት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲን በመተግበር ሂደት በሚኖራቸው ሚና ዙሪያ ተከታታይ አገር-አቀፍ የፓናል ውይይቶችን ማካሄድ፡ (3) | ሴክሬታሪያት፡ የሀይማኖት ተቋማት ምክር ቤት፡ የክልል መስተዳድሮች፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 11. | ለፌዴራልና ክልል መንግስት ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች፡ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ለክልል ምክር ቤት አባላት የፖሊሲውን ይዘት እና የትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (14) | ሴክሬታሪያት፡ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 12. | በሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ለሚገኙ የዞንና የወረዳ ሀላፊዎች የፖሊሲውን ይዘት/የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (28) | ሴክሬታሪያት፡ ከተቋማቱ ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 13. | በአዲስ አበባ/በክልል ደረጃ በሰብዓዊ መብት፡ ግጭት አፈታት፡ የሕግ የበላይነትና ፍትህ ጉዳዮች ላይ ለሚሰሩ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ (awareness, briefing) መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | ሴክሬታሪያት፡ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ ምዕራፍ ሶስት (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 14. | ለፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች የፖሊሲው ይዘትና ትግበራ ሂደትን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (2) | ሴክሬታሪያት፡ ከፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 15. | በሀገሪቱ ለሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ማህበረሰብና ከፍተኛ አመራር የፖሊሲ ይዘት/ትግበራ ሂደቱን በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (10) | ሴክሬታሪያት፡ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 16. | ለዳያስፖራ ማህበረሰብ ተወካዮች የፖሊሲውን ይዘትና የትግበራ ሂደት በተመለከተ ዝርዝር የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች ማዘጋጀት፡ (በአውሮፓ፡ አሜሪካ፡ በአረብ ሀገራት፡ ውስን የአፍሪካ አገራት) (5) | ሴክሬታሪያት፡ ከዳያስፖራ ኮሚሽን እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 17. | በሽግግር ፍትህ ተቋማት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆችና ሌሎች ህጎች ላይ ህዝብ ዝርዝር አስተያየት የሚሰጥበት ከመደበኛው አሰራር የተለየ አገር-አቀፍ የምክክር መድረክ ማዘጋጀት፡ (ለአንድ ረቂቅ ህግ 5 አገር-አቀፍ መድረኮች) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 18. | የፖሊሲ አማራጭ ሰነዱን፡ የህዝብ ምክክርና ግብአት ማሰባሰብ ሂደት ሪፖርት፡ እና የፖሊሲውን አማርኛና እንግሊዝኛ ቅጂ በህትመት እና በድህረ-ገፆች ማሰራጨት፡ | ሴክሬታሪያት፡ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 19. | የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን የትግርኛ፡ ኦሮምኛ፡ አፋርኛ፡ ሲዳምኛ፡ ጉራግኛ እና ሶማሊኛን ጨምሮ - ቢያንስ በአስር አገራዊ | ሴክሬታሪያት፡ ከየክልሎቹ ፍትህ ቢሮዎች ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቋንቋዎች መተርጎም፣ ቅጂውን በህትመት፣ በማህበራዊ ገጾች እና ድህረ-ገፆች ተደራሽ ማድረግ፣ | | | |
| 20. | የሽግግር ፍትህ ሂደትን የሚመለክቱ ትምህርቶችን/መልዕክቶችን የያዙ አጫጭር ተከታታይ ዘጋቢ ቪዲዮዎችን የሚያዘጋጅ የዘርፉ ባለሙያ መቅጠር፣ ማሰማራት፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 21. | በስኬታማ የሽግግር ፍትሕ ትግበራ ሂደት ያለፉ አገራት ተሞክሮን የሚያሳዩ ታሪካዊና ምስላዊ ቅንብር ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (2) | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 22. | የሽግግር ፍትሕን የተለያዩ ጉዳዮችን የተመለከቱ ድራማና ካርቱን አጫጭር ቪዲዮዎች ማዘጋጀት፣ ማሰራጨት፣ (5) | ሴክሬታሪያት፣ | ከምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 23. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች (ተጎጂዎች፣ የፆታዊ ጥቃት ሰለባዎች፣ ተፈናቃዮች፣ አካል ጉዳተኞች ወዘተ) የሚኖራቸውን ሚና የሚገልፅ ዘጋቢ ቪዲዮ ዶክመንታሪ ማዘጋጀት፣<br>ልዩ ሁኔታቸውን ግምት ውስጥ ያስገባ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ማደራጀት፣ ማሰራጨት፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br>ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 24. | ለሚዲያ ተቋማት የሚሰጡ መረጃዎች አይነት፣ መረጃ ስለሚሰጥበት ጊዜ/አግባብ፣ የመረጃ/የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት፣ መረጃ ስለሚሰጠው አካልና ከሚዲያ ተቋማት ጋር የሚኖር ግንኙነትን የሚገዛ ሁሉን-አቀፍ የኮሚኒኬሽን ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ ስራ ላይ ማዋል፣ (1) | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 25. | ከሚዲያ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በመደበኛነት ምላሽ የሚሰጥ ባለሙያ ማዘጋጀት፣ አከራካሪና የብዙሀኑ ሚዲያ ጥያቄ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አንድ ወጥ ምላሽ ማዘጋጀት፣ ማሳወቅ፣ | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |
| 26. | የሚዲያ ተቋማትና ባለሙያዎች ፖሊሲውንና የሽግግር ፍትህ ሂደቱን በተመለከተ የሚያዘጋጇቸው ዘገባዎች በሙሉ እውቀት ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑ ለማድረግ - ለሚዲያ ተቋማት አመራሮች፣ ለዜና እና ፕሮዳክሽን ክፍል ዋና ኤዲተሮች፣ ሪፖርተሮች፣ የመንግስት የህዝብ ግንኙነት አመራሮች፣ ለማህበረሰብ-ዐቀፍ ሬዲዮ ተወካዮችና ለተመዘገቡ ዩቲዩበሮች ተከታታይ ይዘት-ተኮር ስልጠናዎችን፣ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ መስጠት፣ (6) | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 27. | የሚዲያ ተቋማት በሽግግር ፍትህ ሂደቱ ላይ ተከታታይነት ያላቸው የራሳቸው ሳምንታዊ ፕሮግራሞች እንዲቀርፁ ማድረግ፣<br>የተመረጡ ፕሮግራሞችን ማዘጋጀት፣ | ሴክሬታሪያት፣<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፣<br>የሚዲያ ካውንስል፣ | ከምዕራፍ 1፣ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | (በሳምንት አንድ፡ በአመት 52) | | | |
| 28. | በፖሊሲ ትግበራ ምዕራፍ የተከናወኑ ስራዎችን በምስል (ስፖት) ማቀናበር፡ ለሚዲያ ተቋማት መላክ፡ በሽግግር ፍትህ፡ በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆች እና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፡ (26) | ሴክሬታሪያት፡ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፡ | |
| 29. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን የተመለከቱ ጋዜጣዊ መግለጫዎች በአማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች ማዘጋጀት፡<br>ለሚዲያ ተቋማት መላክ፡ በሽግግር ፍትህና በፍትህ ሚኒስቴር ድህረ-ገፆችና ሌሎች ማህበራዊ ሚዲያዎች ማጋራት፡ (12)<br>ጋዜጣዊ መግለጫ ኮንፈረንስ ማካሄድ (4) | ሴክሬታሪያት፡ | ከምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)<br>ጀምሮ፡ | |
| 30. | በሁሉም የሽግግር ፍትህ ሂደት የሰነድና ዜና ዝግጅቶች ላይ የሚሰፍር ቋሚ ታግላይን ማዘጋጀት፡ ጥቅም ላይ ማዋል፡ ("የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ሥርዓት በሀገር መሪነትና ህዝብ ባለቤትነት እውን ይሆናል") (1) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 31. | በመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት ለሚዲያዎች በሚሰጥ ወቅታዊ ጋዜጣዊ መግለጫዎች የሽግግር ፍትሕ ጉዳይ መደበኛ አጀንዳ እንዲሆን ማድረግ፡ ከአመራሮች ጋር ውይይት ማካሄድ፡ ውሳኔ ማሳለፍ፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡ | |
| 32. | የሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደቶች አሁናዊ ሁኔታን በተመለከተ በኢትዮጵያ ለሚገኙ የውጭ አገራት ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች፡ ዓለም-አቀፍ ተቋማትና የልማት አጋሮች መደበኛ የመረጃ ልውውጥ (briefing) መድረኮችን ማዘጋጀት፡ (4) | ሴክሬታሪያት፡<br>ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር፡ | ከምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)<br>ጀምሮ፡ | |
| 33. | የአለም-አቀፍ ወንጀሎች አዋጅ፡<br>- የረቂቅ ዝግጅት፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት፡<br>- የረቂቅ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፡<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፡<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br><br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 34. | የሽግግር ፍትህ ልዩ አቃቤ ሕግ ተቋም ማቋቋሚያ ሕግ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት ስራዎች፡<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን ነጻና ገለልተኛ አድርጎ ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ መለስተኛ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፡ የሃላፊዎች አሿሿም፡ | ሴክሬታሪያት፡<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፡<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፡ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የዐቃብያነ ሕግና መርማሪዎች አሿሿም እና አነሳስ፣ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽህፈት ቤት የስራ ዘመን፣ የልዩ ዐቃቤ ህግ ተቋሙ ስልጣንና ተግባር፣ የበጀት ነፃነት፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር፣ እና በስራ ላይ ያሉ ህጎች ተፈጻሚነት ላይ ያተኮረ)፡<br>- የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋምን አደረጃጀት፣ ስልጣን፣ ተግባር የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ማዘጋጀት፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብር አካልን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤት እና ሰው ኃይል የማደራጀት ስራ፣ | | | |
| 35. | የእውነት ማፈላለግ/ማውጣት፣ የእርቅ፣ ምህረትና ማካካሻ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣<br>- የእውነት ማፈላለግ፣ ይፋ ማውጣት፣ እርቅ፣ ምህረትና ማካካሻ ተግባራትን ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነት እና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን፣ (በዋናነት በተቋሙ አደረጃጀት፣ የሃላፊዎች አሿሿም፣ ለሹመት ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ የኮሚሽነሮች አሿሿም/አነሳስ፣ የስራ ዘመን፣ የተቋሙ ስልጣንና ተግባር፣ የበጀት ነፃነት፣ ከሌሎች ተቋማት ጋር የሚኖረው ግንኙነት/ቅንጅታዊ አሰራር ላይ ያተኮረ)፡<br>- የኮሚሽኑን ስልጣን፣ ተግባራትና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- የተጎጂዎች መልሶ ማቋቋም፣ ዘላቂ ማካካሻ ስርዓት ሕግ ማእቀፍ ማካተት፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣ | ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 1፡<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 2፡<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤትና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፣ | | | |
| 36. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና ተቋማዊ አደረጃጀት፣<br>- ነጻና ገለልተኛ ችሎት ከማቋቋም አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ የዳሰሳ ጥናት ማከናወን (በዋናነት የልዩ ችሎቱ አደረጃጀት፣ ልዩ ችሎቱ የሚያያቸው ጉዳዮች አይነት ዝርዝር፣ ዳኛ ሆኖ ለመሾም ብቁ የሚያደርጉ መስፈርቶች፣ ዳኞችን በተመለከተ ህዝብና ባለድርሻ አካላት ጥቆማ እና አስተያየት የሚሰጡበት/የልየታ እና ማጥራት ሥርዓት፣ የዳኞች ስብጥር፣ በልዩ ችሎቱ በአማካሪነት እና በአሰልጣኝነት የሚሰሩ ባለሙያዎች፣ የልዩ ችሎቱ ሬጂስትራር፣ የተጎጂዎች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ የተከላካይ ጠበቆች ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት፣ ዳኞች የሚነሱበት እና የሚተኩበት ሥርዓት ላይ የሚያተኩር)፣<br>- የልዩ ችሎቱን ስልጣንና ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፣<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር አምስት የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፣<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፣<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማጸደቅ፣<br>- የጸደቀውን ህግ ማስተዋወቅ፣<br>- የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፣ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣<br>ከሴክሬታሪያት፣<br>ፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣<br>እና<br>የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 1፣<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣<br>ምዕራፍ 2፣<br>(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣ | |
| 37. | የህግና ተቋማዊ ማሻሻያ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ዝግጅትና አደረጃጀት፣<br>- የልየታ፣ ማጥራትና ማሻሻያ ስራዎችን ነጻነትን፣ ገለልተኛነትን፣ ተቀባይነትና ተአማኒነትን በሚያረጋግጥ መንገድ ከመተግበር አንፃር የሚጠበቁ አነስተኛ መሪ መርሆችን ይዘት ያካተተ ጥናት/የአውድ ትንታኔ ማከናወን፣<br>- የልየታ፣ ማጥራትና ማሻሻያ ስርዓትን የሚመራ፣ የኮሚሽኑን ስልጣንና | ሴክሬታሪያት፣<br>ከፍትህ ሚኒስቴር፣<br>የሚኒስትሮች ምክር ቤት እና የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በመተባበር፣ | ምዕራፍ 3፣ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፣<br>ምዕራፍ 4፣ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ተግባራት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚደነገግ አዋጅ ማርቀቅ፡<br>- ከባለድርሻ አካላት ጋር 5 የግብዓት ማሰባሰቢያ መድረኮች ዝግጅት ማከናወን፡<br>- የረቂቅ አዋጁ ይዘት ክለሳ፡<br>- የመጨረሻ ረቂቅ ለሚኒስትሮች ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ማስጸደቅ፡ የጸደቀውን ሕግ ማስተዋወቅ፡<br>- አዋጁን የሚተገብሩ አካላትን ማሰልጠን፡<br>- የተቋሙን ፅህፈት ቤትና ሰው ኃይል ማደራጀት ስራ፡ | | | |
| 38. | አዲስ የሚቋቋሙ የሽግግር ፍትህ ተቋማት ፖሊሲውን በሙሉ አቅማቸው ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል የሚከተሉት መሰረታዊ የአቅም ግንባታ ስዎች ይከናወናሉ፡<br>- አዲስ ለሚቋቋሙ ተቋማት አመራሮች በፖሊሲውና ትግበራ ሂደቶች፡ በተቋማት ማቋቋሚያ አዋጆች ይዘት፡ በሌሎች መንግስታዊ ተቋማት ሚና ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፡ (4)<br>- ተቋማቱ ባለሙያዎች ተመሳሳይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች መስጠት፡ (4)<br>- የሽግግር ፍትህ ተቋማትን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ እና በቴክኒክ ሊደግፉ የሚችሉ የልማት አጋሮች እና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችን በዝርዝር መለየት፡ የባለድርሻ አካላት ልየታ (Stakeholdes Mapping) ማዘጋጀት፡ (1)<br>- በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት የልማት አጋሮችና ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚኖራቸው ሚና ላይ ዎርክሾፕ ማዘጋጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br><br>ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 39. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ ሂደት በተለይ የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ዝርዝር ስራዎች ይከናወናሉ፥<br>- የተቋሙ አመራሮች፡ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞችን በዓለም-አቀፍ ወንጀሎች የምርመራና ክስ ቴክኒካዊ አሰራሮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው አማካሪዎች መቅጠር፡ (2) የአማካሪዎች ምልመላ/ሚና ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br><br>የልዩ ዐቃቤ ሕግ ተቋም፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡<br>ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | - በሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ትግበራ፣ በዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ እና ክስ ጉዳይ ላይ ዝርዝር ቴክኒካዊ ስልጠና የሚሰጡ ተቋማት/ባለሙያዎችን መለየት፣ ስልጠናዎች መስጠት፣ (4)<br>- የወንጀል ምርመራና ክስ ስርዓት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ የሚያስችል የወንጀል ምርመራ፣ ክስና ማስረጃ አስተዳደር ስርዓት (Case Management System) ማበልጸግ፣ (1)<br>- ተጎጂ-ተኮር የምርመራና ክስ አሰራርን በተመለከተ የስልጠና ማንዋል ማዘጋጀት፣ (1)<br>- የተቋሙ አመራርና የተመረጡ አቃብያኔ ህጎች በወንጀል ምርመራና ክስ ስራ ሂደት ስኬታማ ታሪክ ባላቸው የአፍሪካና ሌሎች አገራት የስራ ጉብኝት/የልምድ ልውውጥ መርሀ-ግብሮችን ማመቻቸት፣ (3)<br>- የሙብት ጥሰት ሰለባዎችን ጨምሮ ማንኛውም ሰው ባለበት ሆኖ የወንጀል ድርጊት ጥቆማና ማስረጃ የሚያቀርብበት ነጻ የስልክ ጥሪ ማዕከል፣ ድህረ-ገፅ ማደራጀት፣ (1)<br>- የተቋሙን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፣ መረጃዎች፣ የምስክሮች ቃል፣ መዝገቦችና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ዳታ-ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፣ (1) | | | |
| 40. | የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎት አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፦<br>- የፍርድ ቤት ፕሬዝደንቶች፣ የችሎት ሰብሳቢዎች፣ ዳኞች፣ ሬጂስትራሮች፣ ተከላካይ ጠበቆችና የተጎጂዎች ድጋፍ ማስተባበሪያ ፅህፈት ቤት ባለሙያዎችን በዓለም አቀፍ ወንጀሎች የክስና ክርክር መስማት፣ ችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎች መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፣ (1) ቅጥር ማካሄድ፣ (2)<br>- በሽግግር ፍትሕ ሂደት የዓለም አቀፍ ወንጀሎች ምርመራ፣ ክስና ክርክር፣ የችሎት አመራር፣ ውሳኔ አሰጣጥ፣ ተጎጂ-ተኮር የፍርድ ሂደትና ተያያዥ | የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣<br><br>ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 2፣ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፣<br>ምዕራፍ 3፣ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፡ (3)<br>- የችሎት ፕሬዝደንቶች፡ የችሎት ሰብሳቢዎች እና የተመረጡ ዳኞች በስኬት በሚጠቀሱ የአፍሪካና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ በሽግግር ፍትሕ የወንጀል ክስና ክርክር ሂደት፡ የችሎት አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ ጉዳይ ላይ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- የሽግግር ፍትህ ልዩ ችሎቶችና (እንደአስፈላጊነቱ) በየክልሎች የሚደራጁ ምድብ ችሎቶች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማት እንዲደገፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ግብቶችን ማሟላት፡ ለዚህ የሚያስፈልግ የተፈላጊ መሰረተ-ልማት ቴክኒካል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1)<br>- የችሎቱን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችን፡ የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቆየት የሚያስችል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1)<br>- የተቋሙን የስራ ስፋትና ውስብስብነት ታሳቢ ያደረገ በቂ በጀት፡ የሰው ኃይልና ግብዓት ዝርዝር ማዘጋጀት፡ | | | |
| 41. | የእውነት ማፈላለግ፡ ምህረትና ማካካሻ ኮሚሽን አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በጉልህ አለም-አቀፍ ወንጀሎች ምርመራና ክስ፡ በአማራጭ ግጭት መፍቻ መንገዶች፡ የእውነት ማፈላለግና ይፋ ማውጣት ሥርዓት ፡ በምህረትና ይቅርታ አስተዳደር እና ተመራጭ የማካካሻ ስራዎች አካሄድ ላይ ተቋሙን እና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) ቅጥር ማካሄድ፡ (2)<br>- በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና ማዘጋጀት፡ (5)<br>- ኮምሽነሮችና ውስን የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬት በሚጠቀሱ የአፍሪካ ወይም ሌሎች አገራት | ኮሚሽን፡<br><br>ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 3፡ (ታህሳስ-የካቲት 2017 ዓ.ም)፡ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ጉብኝት በማድረግ ከአገራት ወይም ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- ከሰብአዊ መብት ጥሰት ጋር የተያያዙ የታሪክ መዝገቦችን፡ የተጎጂዎች ምስክርነት ቃልና ሌሎች ማስረጃዎችን ለማሰባሰብ እና ለማቀየት የሚያስችል የኮሚሽን ፊዚካል አርካይብ እንዲደራጅ ቴክኒካል መዘርዝር ማውጣት፡ (1)<br>መሰረተ-ልማቱን እና ሙዝየም ማደራጀት፡ (1)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመንና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችና የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ቨርችዋል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1) | | | |
| 42. | የተቋማዊ ማሻሻያ ተቋም አቅም ለማሳደግ የሚከተሉት ስራዎች ይከናወናሉ፡<br>- በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ የሚከናወኑ ተቋማዊ ማሻሻያ ስራዎች ምንነት፡ አስፈላጊነት እና ዝርዝር አካሄድ ላይ ተቋሙንና ሀላፊዎቹን የሚያማክሩ አለም-አቀፍ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን መቅጠር የሚያስችል ጋይድላይን ማዘጋጀት፡ (1) ቅጥር ማካሄድ፡ (1)<br>- ከፍተኛ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች የሚሰጥ ተከታታይና አውድ-ተኮር ስልጠና ማዘጋጀት፡ (5)<br>- ኮምሽነሮችና የተመረጡ የተቋሙ ባለሙያዎች በስኬታማነት በሚጠቀሱ የአፍሪካና ሌሎች አገራት ጉብኝት በማድረግ ከአገራት/ተቋማት ምርጥ ተሞክሮ ልምድ እንዲቀስሙ ማስቻል፡ (3)<br>- የኮሚሽኑን ስራዎች ለማዘመን እና ለህዝብ ተደራሽ ለማድረግ፡ መረጃዎችንና የምስክሮች ቃል፡ መዝገቦችንና ሌሎች ሰነዶችን ሰብስቦ ለማቀየት የሚያስችል ቨርቷዋል ዳታ ቤዝ (እና ድህረ-ገፅ) ማበልጸግ፡ (1) | ተቋም/ኮሚሽን፡<br><br>ሴክሬታሪያት፡ | ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 43. | በሽግግር ፍትህ አተገባበር የክልሎችን ተሳትፎ እና ሀላፊነት ዝርዝር የሚያስቀምጥ ሁሉን-አቀፍ መሪ ሰነድ (Comprehensive Guiding Document) ማዘጋጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፡<br><br>ከክልሎች ጋር የሚፈጥረው ቅንጅታዊ አሰራር፡ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 44. | በክልሎች ደረጃ ጥሰቶች እንዲፈጸሙ ያስቻሉ የሕግ ማዕቀፎችና ቅድሚያ | የክልል ፍትህ ቢሮዎች፡ መስተዳድሮች፡ | ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የሚሰጣቸው ውስን ተቋማትን በተገቢ መልክ ለመለየት፣ ለማጥራት እና ለመለወጥ የሚረዳ ቴክኒካል ሰነድ ማዘጋጀት፣ የተቋማዊ ሪፎርም መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ ትግበራ መጀመር፣ | | ዓ.ም)፡ | |
| 45. | በሽግግር ፍትህ ስራ የሚሳተፉ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓቶች መለያ እና ማሳወቂያ አሰራር፣ የሚኖራቸው ሀላፊነት፣ እና ስራቸውን የሚያከናውኑበትን አግባብ የሚዘረዝር ማንዋል ዝግጅት፡ (1) | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሴክሬታሪያቱ ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 46. | የተመረጡ ባህላዊ የግጭት አፈታት ተቋማትን አቅም የመገንባት ስራ፡ (2 ዙሮች) | ክልሎች እና ከባቢያዊ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ከሴክሬታሪያቱ ጋር የሚፈጥሩት ትብብር፣ | ምዕራፍ 4፡ (መጋቢት-ግንቦት 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 47. | በሽግግር ፍትህ ትግበራ የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎች ተሳትፎ ዝርዝር ስትራቴጂ ማዘጋጀት፣ መተግበር፡ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br><br>ከኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን፣<br><br>የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ እና አጋሮች ጋር በመቀናጀት፣ | ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 48. | የሽግግር ፍትህ ሥርዓት ስራዎች የተጋላጭ ማህበረሰብ ክፍሎችን ድምፅ እና ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ መከናወናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መደበኛ የክትትል ሥርዓት (Monitoring Mechanism) ማዘጋጀት፣<br>መደበኛ የክትትል ስራዎች ማከናወን (2)፡ | የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ቅንጅት፣ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 49. | የሽግግር ፍትህ ተቋማት አደረጃጀት የተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚችል የስራ ክፍል እንዲኖራቸው ማድረግ፡ | ሴክሬታሪያት፣ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣<br><br>ምዕራፍ 2፡ (መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም)፡ | |
| 50. | የወንጀል ተጠያቂነት ስራ ሂደቶች ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ምቹ፣ አሳታፊና ደህንነትን ያስጠበቀ ማድረግ፡<br>ይህን የሚያግዝ ራሱን የቻለ ንኡስ መዋቅር ማደራጀት፡ (1) | ሴክሬታሪያት፣<br><br>ከኮሚሽኖች እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፣ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 51. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፣ የምክር እና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ሁሉን-አቀፍ ዘላቂ አደረጃጀት/ሥርዓት እንዲመሰረት ማድረግ፡<br>የፆታ ጥቃት ሰለባ አገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን (አንድ ማእከሎች፣ ማገገሚያ ተቋማት) ማጠናከር፣<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ መተግበር፣ | ሴክሬታሪያት፣<br><br>ከኮሚሽኖች፣<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፣ | ከምዕራፍ 1፡ (ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 52. | በአጭር ጊዜ በሽግግር ፍትህ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች የስነልቦና፣ ምክርና የህክምና ድጋፍ የሚቀርብበት ጊዜያዊ አደረጃጀት መመስረት፣ ማጠናከር፣ ስራዎችን መተግበር፣ | ሴክሬታሪያት፣<br><br>ከኮሚሽኖች፣<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፣ | ከምዕራፍ 2፣(መስከረም-ህዳር 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 53. | በሽግግር ፍትህ ረጅም ጊዜ ማዕቀፍ ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች ኢኮኖሚያዊ (ራስ-አገዝ) አገልግሎት የሚቀርብበት አደረጃጀት መመስረት፣ ማጠናከር፣<br>መርሀ-ግብሮችን መንደፍ፣ መተግበር፣ | ሴክሬታሪያት፣<br>ከኮሚሽኖች፣<br>የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣<br>እና ሲቪል ማህበረሰብ ጋር በመቀናጀት፣ | ከምዕራፍ 5፣ (ሰኔ-ነሃሴ 2017 ዓ.ም) ጀምሮ፣ | |
| 54. | የመረጃ መሰረተ-ልማት ግንባታ<br>ሀ) ድህረ-ገፅ እና ማህበራዊ ሚዲያ፣<br>- የሽግግር ፍትሕ አገር-አቀፍ ስራዎችን ሂደት፣ ረቂቆች፣ ቃለ-ጉባዔዎች፣ የምክክር ሂደቱ የምስልና የድምጽ ሪከርዶች፣ ዋና ዋና ሰነዶች፣ ዘገባዎችና ወቅታዊ ሪፖርቶችን የሚይዝ ድህረ-ገፅ ስራ ማጠናቀቅ፣ ከአልሚው መረከብ፣<br>- ለዚሁ ዓላማ ከፍተኛ አቅም ያለው ሰርቨር ኪራይ መፈጸም፣<br>- ድህረ-ገፁን እና ሌሎች ለሽግግር ፍትህ ዓላማ የሚከፈቱ የመረጃ ማከማቻ እና ማጋሪያ ዘዴዎችን የሚያስተዳድር፣ በየወቅቱ በአዳዲስ መረጃዎች የሚያደራጅ የሚከታተል፣ ከፍተኛ ብቃት ያለው ቋሚ የዘርፍ ባለሙያ መቅጠር፣ መመደብ፣<br>- ተመሳሳይ መረጃዎችን በተመጠነ አግባብ በፌስቡክ እና ትዊተር ገፆች ላይ ማሰፈር፣<br>- የሽግግር ፍትህ ሂደት ዋና ዋና መረጃዎችን በማእከላዊነት የሚይዝ ትልቅ አቅም ያለው መጠባበቂያ የውጭ ቋት (external database/ backup drive) ማዘጋጀት፣<br>ለ) አርካይቭ<br>- የሽግግር ፍትህ ስራ ሂደቶችን የሚመለከቱ የተመረጡ በወረቀት የተዘጋጁ መሰረታዊ ሰነዶች ሚስጥራዊነትና ደህንነትን ለመጠበቅ የሚያስችል ማእከላዊ የአርካይቭ ሥርዓት ማደራጀት፣ ለዚህ የሚያገለግሉ ፅህፈት-ቤትና ቁሳቁሶችን ማዘጋጀት፣<br>ሐ) ሙዚየም<br>- የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲውን ዝግጅት ሂደት እና የትግበራ ስራዎችን በተሟላ መልኩ የሚገልፅ በየጊዜውም እየተሟላ የሚሄድ ማሳያ (ሙዝየም) ሴክሬታሪያቱ | ሴክሬታሪያት፣ | ምዕራፍ 1፣<br>(ሰኔ-ነሀሴ 2016 ዓ.ም)፣ | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | **በሚገኝበት የፍትሕ ሚኒስቴር ህንፃ ውስጥ እንዲደራጅ ማድረግ፡** | | | |
| | | | | |